# ጉባኤ ቃና

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ለግቢ ጉባኤ ተማሪዎች

ጉባኤ ቃና ፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፩

ሐምሌ ፳፻፲፯ ዓ.ም



"ያለሥራ የሚያልፍ ጊዜ
መኖር የለበትም ::"
ዶክተር ወርቁ ደጀኔ

# ጉባኤ ቃና

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ለግቢ ጉባኤ ተማሪዎች

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን በግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ በትምህርትና ሚዲያ ዋና ክፍል በተለይ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ለግቢ ጉባኤያት) በየሦስት ወሩ እየተዘጋጀ የሚወጣ መንፈሳዊ መጽሔት፡፡

የካቲት ፳፻ ዓ.ም. ተጀመረ

አሳታሚ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/በሰ/ት/ቤቶች ማ/መ/ ማኅበረ ቅዱሳን

011 8 68 47 19 / 011 1 11 88 07/



ከፍተኛ ሪፖርተር

ዲ/ን አበበ ፍቅሬ

የገጽ መልክ/ሌይ አውት/ እና የሽፋን ገጽ ዲዛይን

ልደት አሰፋው

## ማውጫ

**መልእክት**

“በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር”...2

**ስብከት**

“እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?››........5

**ትምህርተ ሃይማኖት**

**“ደምፀ እገሪሁ ለዝናም፤ የዝናም ኮቴው ተሰማ”** ...............................15

**እንግዳችን**

ዕውቀት፣ እምነትና መሪነት..........................31

**የጥያቄዎቻችሁ መልስ**

..............................................................42

**ኪነጥበብ**

ክረምቱን በምን?.................................46

ማኅበረ ቅዱሳን እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህንን ስያሜ አግኝቷል፡፡

# “በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር”

(2ኛ ጢሞ. ፫፥፲፬)

ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ ሲመክረው የተናገረው ቃል ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ሲያገለግል በሥጋ ፍላጎት ያሉ ሰዎች እንዴት እንደተቃወሙት በአገልግሎቱ ላይ ምን ያህል ጫና እንዳደረሱበት እያወሳ በእርሱ ጫና እንዳደረሱ በጢሞቴዎስ ላይ እንደሚያደርሱበት ያውቃልና ይህንን ምክር መከረው፡፡

“ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና” እያለ ያስተማረው እርሱ በመከራ ያለፈ እንደሆነ ጢሞቴዎስም እንደቅዱስ ጳውሎስ፣ “እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ” እንዲል (1ቆሮ. ፲፩፥፩) ቅዱስ ጳውሎስን መስሎ መከራውን ማለፍ እንደሚገባው ሲያስገነዝበው ነው፡፡ በዚህ በመምሰል ውስጥ ደግሞ መከራ አለ፡፡ (፪ጢሞ. ፫፥፲፪)

አገልሎቱን የሚያደናቅፉት ኢአማንያን ብቻ አይደሉም “አማኝ ነን” ብለው የሚያስቡ ነገር ግን ሥጋዊ ምኞታቸው ያሸነፋቸው፣ ከፖለቲካው የሚዶልቱ፣ በዘረኝነት ወላፈን የነደዱ “በበግ ለምድ ሚመትና ልብስ ተሰውረው በቤቱ የሚርመሰመሱ ይኖራሉ “የአምልኮ መልክ አላቸው ኀይሉን ግን ክደዋል” እንዲል፡፡ (፪ጢሞ. ፫፥፭) በእኛ ዘመን ብቻ ያለ ሳይሆን ገና ከጥንት ጀምሮ መኖሩን ሐዋርያው “ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴን እንደተቃወሙት” ገልጾለት የሚሸነፉበትንም ሲነግረው “አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ፍቅሬንም

መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ" እያለ "የእግዚአብሔር ዕቃ ጦር" አስታጠቀው (ኤፌ. ፮፥፲፩)

በግቢ ጉባኤ ቆይታችሁ የተማራችሁትን ትምህርት ወደመጣችሁበት ስፍራ እንዴት እንደምታደርሱ፣ የሚገጥሟችሁን ፈተና ሁሉ በጽናት ተወጥታችሁ የያዛችሁትን ዘር ዘርታችሁ ሠላሳ ስሳና መቶ እንዲያፈራ የምታደርጉበት ጊዜ አሁን ነውና ከግቢ ጉባኤ እንዴት እንደተጠራችሁ ታውቃላችሁና።

የቤተ ክርስቲያንን መዋቅር በደንብ ተረድታችሁ በተረዳችሁት የተግባቦት ክሂሎት አጋር ማኅበራት፣ አጥቢያ፣ ቤተ ክህነትና ሌሎች በየደረጃው ከሚገኙ የቤተ ክርስቲያናችን መዋቅር ጋር በመሆን ሥራዎችን ለመሥራት ታጥቃችሁ መነሣት ይጠበቅባችኋል።

በአገልግሎት ጊዜ መሰናክል ቢገጥማችሁ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋራ በመነጋገር አካሄዶችን ከሌሎች የልምድ ተሞክሮ በመቅሰም በትዕግሥትና በጽናት ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን መፍትሔ ለማምጣት መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በዚህ መልኩ የክረምት እረፍታችሁን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰጥታችሁ በነፍስም በሥጋም ልትጠቀሙ ይገባል።

# ‘‘እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?

በዲ/ን ማለደ ዋሲሁን

ጾም ማለት ከምግብ መቆጠብ ወይም መከልከል ማለት ነው፡፡ በነጠላ ትርጉሙ ከምግብና ከመጠጥ ለተወሰነ ጊዜ መቆጠብ፣ የእንስሳት ተዋጽኦ ከሆኑ ምግቦች ለጊዜው መታቀብ ማለት ነው፡፡ ክርስቲያናዊ በሆነው መንፈሳዊ ሕይወት ግን መጽሐፍ ቅዱስንና የቀደሙ አባቶቻችንን የአኗኗር ትውፊት መሠረት አድርጎ የሚኖርን የጾም ሕይወት ያመለክታል፡፡ ለምሳሌም ሙሴ አርባ ቀን ጾመ፣ ጌታችንም በምድረ በዳ አርባ ቀን ጾመ (ማቴ.፬፥፪) የሚለውን እናገኛለን፡፡ እነዚህን መሠረት አድርጎ ጾም ሲተረጎም ግን ነቢዩ “እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?›› (ኢሳ.፶፰) ብሎ የተናገረለትን የጾምን ምሥጢራዊ (መንፈሳዊ) ትርጓሜ እናገኛለን፡፡

በምሥጢራዊ ትርጓሜ ጾም ከምግብ መቆጠብ ብቻ አይደለም፤ ከኃጢአት መቆጠብም ነው፡፡

እንግዲህ በመንፈሳዊ አስተምህሮ ጾም ማለት፦

- ከክፉ አሳብ መቆጠብ
- ከክፉ ንግግር መቆጠብ
- ከኃጢአት ሁሉ መራቅ
- በአጠቃላይ ለጸሎት፣ ለንስሓ፣ ለምጽዋት የምንተጋበት ጊዜ ማለት ነው፡፡

ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሔር የሚወደው እውነተኛ ጾም ሥጋን ለመግዛት በአካለ ሥጋ የምንጾመውና ነፍሳችንን ከኃጢአት ርኵሰት ለመጠበቅ የምናደርገውን ተጋድሎ ያካተተ ነው፡፡

የጾም ዓላማዋ ነፍስን ማዳን ነው፡፡ ቅዱስ ያሬድ ‹‹ጾም ትፌውስ ቊስለ ነፍስ፤ ወታጸምም ኲሎ ፍትወታተ ዘሥጋ፤ ወትሜህሮሙ ጽሙና ለወራዙት፤ ጾም የነፍስን ቊስል ትፈውሳለች፤ የሥጋን ፍትወታት ሁሉ ታጠፋለች፤ ለወጣቶችም ትሕትናን ታስተምራለች፡፡›› ያለው ይሄንኑ ሲያስገነዝበን ነው፡፡

ዓለማውያን በጾም ቆይታ ያደርጋሉ፤ የሚጾሙበት ዓላማ ግን ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ጾም ሥጋቸውን ለማክሳት፣ የሥጋቸውን ጤና ለመጠበቅ፣ ሌሎች ግላዊና ባህላዊ ምክንያቶች ሊያስጾሟቸው ይችላሉ፡፡

እውነተኛው ጾም ግን ዓላማው የነፍስ መፈወስና መዳን ነው፡፡ በመጽሐፈ መነኮሳት የተጻፈውን እናስተውል ‹‹ጾም ቊስለ ነፍስን የምትፈውስ፤ ኃይለ ፍትወትን የምታደክም፤ የበጎ ምግባራት ሁሉ መጀመሪያ፤ ከእግዚአብሔር ጸጋን የምታሰጥ፤ የወንጌል ሥራ መጀመሪያ፤ የጽሙዳን ክብራቸው፤ የደናግል የንጽሕና ጌጣቸው፤ የዕንባ መፍለቂያዋ፤ አርምሞን (ዝምታን) የምታስተምር፤ ለበጎ ሥራ ሁሉ የምታነቃቃ፤ ሰውነትን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ ትሕትናን ገንዘብ ለማድረግ የምትረዳ መድኃኒተ ነፍስ ናት፡፡››(ማር ይስሐቅ አንቀጽ ፬ ምዕ. ፯)፡፡

እኛ በሥጋችን የምንጾመው ራስን ለመግዛት የነፍስ ፈቃድን ለማሠልጠን እንዲያግዘን እንጂ በራሱ ሥጋን ማስራብ ግብ ሆኖ አይደለም፡፡ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግለን ነው፡፡ “አሁንስ ይላል እግዚአብሔር፤ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡” (ትንቢተ ኢዮኤል ፪፥፲፪) እንዳለ፡፡

# የዐዋጅ ጾም

ጾም ሲባል ክርስቲያኖች በራሳቸው ፈቃድ የሚጾሙት ብቻ ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያን አባቶች በሠሩት ሥርዓት መሠረት በዐዋጅ ይጾማል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ የሚጾሙ ሰባት የዐዋጅ አጽዋማት አሏት፡፡

በአንድነት የመጾሙ አስፈላጊነት መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊና የእግዚአብሔር ሕዝብ ሥርዓት ሆኖ የኖረ በመሆኑም ነው፡፡

እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርና መገዛት የሚገልጹት በግላቸው በሚኖራቸው የእምነት ሕይወት ብቻ አልነበረም፡፡ እንደ አንድ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፍቅርና መገዛታቸው ጾምን በማወጅ በጋራም በመዘመር ይገልጹ ነበር፡፡ ሰዎች በጋራ እንደሚጸልዩት በጋራ እንደሚዘምሩት በጋራ መጾማቸው ተገቢና ሥርዓታዊ ሆኖ የኖረ ነው፡፡ ነቢዩ ኢዩኤል ፪፥፲፪-፲፭ "መለከት ንፉ… ጾም ቀድሱ፤ ጉባኤን ሰብስቡ" ያለው ይህን ያስታውሳል፡፡

ክርስቲያኖች ለአንድ የአገልግሎት ዓላማም መሳካት አበክረው በጋራ ይጸልዩ ነበር፡፡ ይህንን መንፈሳዊ ተግባር የተማርነው ደግሞ ከመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ በዘመነ ሐዋርያት ‹‹እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ፡፡ በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው፡፡›› (ሐዋ. ፲፫፥፪-፫) እንደተባለ ለአገልግሎታቸው ሁሉ መቃናት እና መባረክ በጋራ ይጸልዩ ነበር፡፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሕዝቡ መካከል ተመላልሶ የማስተማር ሥራውን ለመጀመር ሲዘጋጅ ከጥምቀቱ በኋላ በገዳመ ቆሮንቶስ አርባ ቀን፣ አርባ ሌሊት መጾሙን ከወንጌል

እናነባለን። እኛም ከበዓላት ክብር በፊት ከትንሣኤው፣ ከበዓለ ልደቱ ወዘተ. በፊት መጾማችን ጥያቄ የሚያስነሣ አይሆንም።

ከዚህ ባሻገርም በጋራ በዐዋጅ መጾም ክርስቲያኖች የአንድ የክርስቶስ የአካሉ ብልቶች እንደመሆናቸው ከእርሱም ጋር ያላቸውን ኅብረት የሚገልጹበት፣ የሚያጸኑበት ነው። እንደ አንድ አካል ‹‹እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።›› (፩ኛ ቆሮ. ፲፪፥፲፫) እንደተባለ።

ለአንዳንዶች በጋራ መጾም የፈሪሳውያን አካሄድ የሚመስላቸው አሉ። ፈሪሳውያንን ያስነቀፋቸው የሚጾሙበት መንገድና ዓላማ እንጂ መጾማቸው ወይም በዐዋጅ መጾማቸው አልነበረም። ለታይታ መጾም፣ ለአድማና ለጥላቻ፣ ሰውንም ለማጥፋት መጾም በእጅጉ የሚነቀፍ ጾም ነው። አስቀድሞ ከጠቀስነው ለነፍስ ዓላማ ከሚጾመው እውነተኛው ጾም በተለየ መንፈስ ይጾሙ ስለነበር የፈሪሳውያን ጾም የተወገዘ ነው።

## ለምን አብዝተን እንጾማለን?

ክርስቲያን ለሥጋው ሳይሆን ለነፍሱ የሚያደላ፣ ሥጋን በነፍሱ ለማስገዛት በየጊዜው ሁሉ ተጋድሎ ላይ ያለ ሰው ነው። ስለዚህ ለሚቻለው አብዝቶ መጾም የሚያስነቅፍ አይደለም። አብዝቶ ለወራት መጾም በነቢያት ሕይወት ሕግን ለመቀበል አርባ ቀን የጾመው የሙሴን (ዘጸ. ፴፬፥፳፰)፣ ወደ ኮሬብ ሲጓዝ አርባ ቀን የጾመው የኤልያስን (፩ኛ ነገ. ፲፱፥፰) ጾም እናያለን። በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአርአያነት አርባ ቀን እና አርባ ሌሊቶችን መጾሙን እንመሰክራለን። (ማቴ. ፬) ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እያሉ ብዙ ፈተናዎችን ለማሸነፍ፣ ብዙ መጾማቸው የሚያስነቅፍ አይሆንም። የሚያስነቅፈው ዓላማው የነፍስ ያልሆነ ከንቱ መጠውለግና ከንቱ የጾም ርዝማኔ ነው።

እንደ እኛ እንደሥጋውያኑ የዚህን ዓለም መብል መጠጥ ሳያስፈልጋቸው በዝማሬ ብቻ በሚኖሩ በመላእክት ሥርዓት ለመኖር

ሰማያዊውን፣ መንፈሳዊውን ዓለም የሚናፍቁ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት የሚቻላቸውን ያህል የመጾም ፈቃድ አላቸው፡፡

አንዳንዶች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድኅነትን ከሠራልን፣ ከሰጠን በኋላ ለምን እንጾማለን ይላሉ፡፡ ክርስቶስ ድኅነትን የሰጠን እንዳንዘምር፣ እንዳንጸልይ፣ እንዳንጾም እንዳንሰግድ፣ ወዘተ. አይደለም፡፡ ሰዎች የዳኑት ከዘለዓለማዊ ውድቀት ከኃጢአት እስራት ነው፡፡ ስለዚህ የተሰጠንን የመዳን ጸጋ አክብረን ጠብቀን ልንኖር የምንችለው በቅድስና ሕይወት ውስጥ ተጠብቀን ጸንተን ስንኖር ነው፡፡ ‹‹የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፡፡›› (፩ኛ ጴጥ. ፩፥፲፮) እንደተባለ ጾም ለቅድስና ሕይወት የሚያበቃ ነው፡፡ ጾም ከሥጋ ሥራ ሁሉ እንድንሸሽ ፈጽመን እንድንርቅም የሚያግዝ ነው፡፡ ለዚህም ሥጋን ማሸነፍ፣ መግዛት ያስፈልጋል፡፡ ‹‹ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ፡፡›› (፩ኛ ቆሮ. ፱፥፳፯) ብሎ ሐዋርያው እንደተናገረ ሥጋን በፈቃዱ መጎሰም የሚቻልበት አንዱ መሣሪያ ደግሞ ጾም ነው፡፡ በጸጋው እንደዳንን የመሰከረው፣ ያስተማረው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚመክረን የሚያስተምረን በጾም እንድንጸና እንድንበረታ ሥጋችንን እንድንጎስም እንጂ ጾምን እንድንሸሽ አይደለም፡፡

ሥጋንም መጎሰም ቢሆን ሥጋን የሚጠቅመው እንጂ የሚጎዳው አይደለም፡፡ በመብልና በመጠጥ መወሰድ፣ በመቀማጠል መኖር የጤና፣ የሥነልቦና፣ አካላዊና አእምሯዊ ችግሮችን ስለሚያስከትል በጾም መጎሰም ከእነዚህ ችግሮችም ያድናል፡፡

ሐኪሞችም ጭምር ጾምን ከደዌ ሥጋ ለመዳን ከሚሰጡት ምክር አንዱ ሆኗል፡፡ ሰዎች ከፍስክ ምግቦች ይልቅ የጾም ምግቦችን(አትክልት፣ ፍራፍሬ) እንዲያዘወትሩ መምከራቸው የታወቀ ነገር ነው፡፡

**ክርስቲያኖች ለአንድ የአገልግሎት ዓላማ መሳካት አበክረው በጋራ ይጸልዩ ነበር፡፡ ይህንን መንፈሳዊ ተግባር የተማርነው ደግሞ ከመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡**

## ጾምና የዩንቨርሲቲ ተማሪነት

ክርስቲያን ወጣቶች መቼም መች በየትኛውም ሥፍራ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መሠረት መጾም ግዴታቸው ነው፡፡ ይህ ማለት በሁሉም ቦታና ሁኔታ ውስጥ ጾምን መጾም ቀላል ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ እጅግ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ሆነው ጾምን በብዙ ተጋድሎ የሚጾሙ ክርስቲያኖችም አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም በተለያዩ ዩንቨርሲቲዎች በትምህርት ዓለም ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በጾም ወቅት ብዙ ፈተናዎች አሉባቸው፡፡

የመጀመሪያው ፈተና የጾም ምግብ ያለማግኘት ነው፡፡ ብዙ ዩኒቨርሲቲዎች ካፌቴሪያዎቻቸው የጾም ምግብ ለማዘጋጀት የሚግደረደሩ፣ አንዳንዶቹም የማይፈቅዱ ናቸው፡፡ ቢፈቅዱም በዓይነትና

በመጠን ጫና የሚያሳድሩ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከቤተሰባቸውና ሊያግዛቸው ከሚችል ማኅበረሰብ ርቀው የሚማሩ ስለሆነ በእነዚህ ዓይነት ያለፈቃዳቸው ከእምነት ሥርዓታቸው እንዲያፈነግጡ በሚያስገድዱ ሁኔታዎች ውስጥ ያልፋሉ፡፡

በሁለተኛነት ደግሞ በዚህ ዐውድ ውስጥ እያሉ በተጨማሪነት ሊያጋጥማቸው የሚችለው የኢ-አማንያን ግፊት ነው፡፡ ‹‹ለምን ትጾማላችሁ?›› በሚለው ጥያቄ ተማሪዎች በከንቱና ያለዋጋ የሚጾሙ እንዲመስላቸው የሚደረግባቸው ጫናና ግፊት ቀላል አይሆንም፡፡ የሚጾሙ ተማሪዎች ከማያምኑ አቻዎቻቸው ጋር ሲኖሩ በሳቅ ስላቅ፣ በንቀትና፣ መጾማቸውን በማጣጣል የሚያደርሱባቸው ግፊት ከፍተኛ ነው፡፡

ከዚሁ ባልተናነሰ የትምህርቱ ጫና የሚያሳድረው ግፊትም ቀላል አይሆንም፡፡ እየጾሙ ረጅም ሰዓት ማጥናትን፣ በቤተ መጻሕፍት ማምሸት ማደርን በተለይ በፈተናዎች ጊዜ ከሚፈጠር ውጥረት ጋር ጾምን አጥብቆ መያዝ ለተማሪዎች ከባድ ፈተና ይሆንባቸዋል፡፡

ሌላው ፈተና በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተማሪዎች ጾምን ለማክበር ፈተና የሚሆንባቸው ከመንፈሳዊ ምክርና ድጋፍ ርቀው የሚገኙ ሲሆን ነው፡፡ ተማሪዎች ከቤተሰብ እና ከቤተ ክርስቲያን አባቶች በራቁ ግቢዎች ሲማሩ ከባድ የመንፈሳዊ ድጋፍ እጥረት ያጋጥማቸዋል፡፡ ማበረታቻ፣ ምክር፣ ተግሳጽና ማጽናኛ ቃልን በቀላሉ ማግኘት አይችሉም፡፡

በአጠቃላይ በእነዚህና መሰል ምክንያቶች በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ መጾም ለተማሪዎች ከባድ ቢሆንም ይህንን ተሻግረው አሸናፊ ሆነው የሚወጡ ንቁ ተማሪዎች ግን በየግቢ ጉባኤያት አሉ፡፡ አንዳቸው ሌላቸውን በማነጽና በማበርታት ለመጾም የሚያደርጉት ተጋድሎ በእግዚአብሔር ፊት ክብር የሚያገኙበት ይሆናል፡፡

ለእነዚህ ተማሪዎች ተጋድሎ ደግሞ ጽናት ከሚሰጧቸው ታሪኮች መካከል አንደኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪካቸውን የምናነበው ስደተኞቹ ዳንኤልና ሦስቱ ወጣቶች ናቸው፡፡

ዳንኤልና ሦስቱ ወጣቶች ከሀገራቸው ከይሁዳ በንጉሥ ናቡከደነጾር ምርኮ ወደ ባቢሎን ተወስደው ሳለ፣ ንቁ ወጣቶች ስለነበሩ ንጉሡ ወደእርሱ ያቀርባቸው ነበር፤ በቤተ መንግሥቱ አካባቢ ከሚቀርበው ማዕድም እንዲሳተፉ ይጋበዙ ነበር፡፡ ይህ ማዕድ ግን ለጣዖታት የሚሰዋ ያማረ እንጀራና የወይን ጠጅ ነበር፡፡ እግዚአብሔር አምነውና ፈርተው፣ የጥበብ መጀመሪያም እግዚአብሔርን መፍራት መሆኑን አውቀው ለሚኖሩ ወጣቶች ይህንን ምግብና መጠጥ መውሰድ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ(ሕግ) አለማክበር መሆኑን አምነዋል፡፡ ስለዚህ በፈቃዳቸው ስለእግዚአብሔር ጾምን መርጠዋል፡፡ ስለዚህ ለጾማቸው የሚገባውን ብቻ ይበሉ ነበር፡፡

በዚህ ስጋት የገባው መጋቢያቸውንም ለጾም በመረጡት ምግብ ሳይጎዱ፣ እርሱንም ሳያስወቅሱት መኖር እንደሚችሉ ገልጸውለት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ለዐሥር ቀናትም ፈተናቸው፡፡ (ዳን. ፩፥፲፪) እነዚህ ወጣቶች በባዕድ ሀገር ቢሆኑም፣ በእምነት የሚመስሏቸው ሌሎች በሌሉበት ዐውድ ውስጥ ጾማቸውን እየጾሙ፣ ሥርዓት ጠብቀው በመኖር የመንፈሳዊ ሕይወታቸውን ልዕልና አሳዩ፡፡ በዚህም ለምልመው፣ አምረውና ተውበው ታዩ እንጂ አልጎሰቆሉም፤ አልጠወለጉም፡፡ በእነርሱ ላይ በሆነው ሁሉ መጋቢያቸው እስኪገረም ደረሰ፡፡

ዳንኤልና ሦስቱ ወጣቶች አስጨናቂውን ጠባይና መንገድ መረጡ፡፡ ከመንግሥት ሰዎችና ከኢአማያን የደረሰባቸውን ጫና ሁሉ ተቋቁመው ከርኵሰት ራሳቸውን ጠበቁ፡፡ ጾም ተራ ከምግብ የመቆጠብ ሥርዓት ብቻ ሳይሆን በማይመች ሁኔታና አካባቢ ውስጥ ሁሉ ለእግዚአብሔር

ያለንን ታማኝነት ጽናት የምናሳይበት መፈተኛ መሆኑንም አስመሰከሩ፡፡

ከዐሥር ቀናት በኋላ እነዚህ ወጣቶች የቤተ መንግሥቱን ምግብና መጠጥ ሲበሉና ሲጠጡ ከቆዩ ሰዎች በላይ ጤናማና ጠንካሮች ሆነው ተገኙ፡፡ ይህም በመጾማችን ለእግዚአብሔር ያለንን ታዛዥነት በረከትን እንደሚያሰጠን ያሳያል፡፡ (ዳን. ፩፥፲፭)

በመሆኑም ለኦርቶዶክሳውያን በተለይ ዓለማዊ ትምህርት በሚሰጥባቸው፣ ብዙ ዓይነት ማኅበረሰብ በሚኖርበት ዩኒቨርሲቲዎችን በመሰሉ አካባቢዎች ለሚኖሩ ወጣቶች የእነዚህ የአራቱ ታማኝ ወጣቶች ታሪክ የምንጊዜም መማሪያ ነው፡፡

ጾማችን ባህሎችን ሁሉ የሚሻገር መንፈሳዊ ሥርዓት ነው፡፡ ስለዚህ በባዕድ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ለእግዚአብሔር ታምኖ ለመገኘት የሚያበረታ ነው፡፡

ይህ ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ በየዕለቱ በሕይወታችን ውስጥ በሚቀርቡልን ጥቃቅን ምርጫዎች ውስጥም ታማኝነታችንን ማሳየት እንደሚቻል ያስተምራል፡፡ ወጣቶቹ የተናቀውን ምግብ በመምረጥ የማኅበረሰብና ባለሥልጣናትን ሁሉ ግፊት በመቋቋም መንፈሳዊ ጽናትን በሕይታቸው ገንብተዋል፡፡ እግዚአብሔርም ይህንን መገዛት፣ መታዘዝ፣ መታመንና ንጽሕና ዳንኤልን በማጽናት፣ ወጣቶቹን በመባረክ ዋጋ እንዳለው አሳይቶናል፡፡ ይህም ዛሬ ላይ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ሆነው ጾማቸውን በታማኝነት ለሚጾሙ ኦርቶዶክሳውያን ወጣት ተማሪዎችና አስተማሪዎች ጥንካሬና በረከት እንደሚሰጥ የሚያረጋግጥልን ነው፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# “ደምፀ እገሪሁ ለዝናም፤ የዝናም ኮቴው ተሰማ”

(ቅዱስ ያሬድ)

በመ/ር ተፈሪ መንገሻ (BTH)

## 1. “ደምፀ እገሪሁ ለዝናም፤ የዝናም ኮቴው ተሰማ” (ቅዱስ ያሬድ)

ቅዱስ ያሬድ ድርሰቶቹ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሥርዓተ አምልኮ ሂደት ውስጥ ትልቁን ሚና የሚወስድ ታላቅ ሊቅና ቅዱስ አባት ነው:: ዓመትን በአራት ዐበይትና በብዙ ንዑሳን አዝማናት ከፍሎ ለእያንዳንዳቸው ስያሜ የሰጠ፤ የዜማ ድርሰቶቹም ሂደት ከኢትዮጵያ አካባቢዎችና የአየር ጸባይ ሁኔታዎች ጋር የተሰናሰለና እነሱንም በምሥጢርና በመንፈሳዊ ሁነቶች በማቆራኘት የገለጠ ነው:: ከአራቱ ክፍላተ ዓመት አንዱ የሆነው ክረምት ነው::

### 1.1.ክረምት በቅዱስ ያሬድ እይታ

ቅዱስ ያሬድ በዚህ የክረምት ወቅት መጀመሪያ ላይ “ደምፀ እገሪሁ ለዝናም፤ የዝናም ኮቴው ተሰማ” በማለት ይናገራል:: ይህም የዝናምን መውረድ የክረምት ወቅትን መግባት የምንረዳበት እና በፍጥረታት ውስጥ የፍጥረታት ፈጣሪ እግዚአብሔርን የምንመለከትበት መነጽር ነው::

ቅዱስ ያሬድ የዚህን የዝናምን መውረድ የውኃ ከላይ የመውረድ ሂደት ብቻ ሳይሆን ወደ ምድር ወርዶ ከሚያከናውነው ሥራና

ከሚያስገኘው ጥቅም አንጻር ሲገልጽ "ደምፀ እገሪሁ ለዝናም ሶበ ይዘንም ዝናም ይጸግቡ ርኁባን፤ ወይትፌሥሑ ነዳያን፤ ወሠርዐ ሰንበተ ለሰብእ ዕረፍተ፤ የዝናም ኮቴው ተሰማ ዝናብ በዘነበ ጊዜ ረኀብተኞች ይጠግባሉ፤ ድሆች ደስ ይሰኛሉ፤ ሰንበትን ለሰው ዕረፍት ፈጠረ" በማለት ይናገራል። (ድጓ ዘክረምት)

መጽሐፍ ቅዱስ ስለዝናብ በልዩ ምሥጢራዊ ሁኔታ ይገልጸዋል። ሙሴ እግዚአብሔር በወቅቱ ዝናብን ለፍሬ እንደሚሰጥና ነገር ግን ያ ሰው በእንጀራ ብቻ እንደማይኖርና ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገርም ሁሉ እንደሚኖር ይናገራል። (ዘዳ. ፲፩፥፲፬)

ስለሆነም ዝናብ ለሥጋ ምግብ ይሆን ዘንድ ብቻ የሚሰጥ ስጦታ ሳይሆን ጸጋን የተጠማች ነፍስም እንደምትረካ የሚያሳይ ምስል ነው። ምድር ያለ ዝናብ ምግብን ወይም ሕይወትን እንደማትሰጥ ሁሉ የሰው ልብም ያለ መለኮታዊ ስጦታ (መጎብኘት) ቅድስናን ሊሠራ አይችልም። ቅዱስ ዳዊት ምድር ያለ እግዚአብሔር በእራሷ ባዶ እንደሆነች፣ የእግዚአብሔር መጎብኘት እንደሚያስፈልጋት "ሐወጽካ ለምድር ወአርወይካ ወአብዛኀኮ ለብዕላ ፈለገ እግዚአብሔር ምሉዕ ማያተ፤ ምድርን ጎበኘሃት አጠጣሃትም፥ በረከተዋንም እጅግ አበዛኅ፤ የእግዚአብሔር ወንዝ ውሀን የተመላ ነው።" በማለት ስለ እግዚአብሔር ጉብኝትና በረከት ይናገራል። (መዝ. ፷፭፥፱) ስለዚህ ነፍስም እንዲሁ የእግዚአብሔር መጎብኘት ማወቅና መጠበቅ እንደሚገባት የሚያሳይ ነው።

ቅዱስ ያሬድ "የዝናብ ኮቴው ተሰማ" ብሎ ሲናገር እግዚአብሔር እኛን ለመጎብኘት እንደሚመጣ እንድናስብና ድምፁን እንድንሰማ የሚያዘጋጀን ነው። በኦሪት ዘፍጥረት ላይ አዳም ከበደለ በኋላ በዚያው ጊዜ በገነት መካከል የእግዚአብሔርን ድምፅ እንደ ሰው እግር ኮቴ ሲመላለስ ሰምቶ ነበር፤ (ዘፍ. ፫፥፰) ስለሆነም በዝናብ

ውስጥ ያሉት የእግር ዱካዎች የእግዚአብሔር መለኮታዊ ጥበቃው ታምኖ የሚቀርብ መሆኑን ያስታውሰናል። ዝናብ በአንድ ጊዜ በኃይል ሆኖ እንደሚደፋ ውኃ በቅጽበት አይወርድም። ምድር እስክትረሰርስ ድረስ በመጠን ይወርዳል እንጂ። አምላክ ለሰው ልጅ የሚሰጠው መለኮታዊው እንክብካቤም እንዲሁ ነው።

ባለጸጋዎች በሀብታቸው ሸምተው ይመገባሉ ነዳያን ግን የሰማይን ጠል የምድርን ቡቃያ ይናፍቃሉ። ስለዚህም በድርቅ ጊዜ ከባዕለጸጋዎች ይልቅ የሚቸገሩት ድሆዎች ናቸው። ለዚህም ነው ቅዱስ ያሬድ "ዝናብ በዘነበ ጊዜ ረኀብተኞች ይጠግባሉ፤ ድሆች ደስ ይሰኛሉ" በማለት የተናገረው። እግዚአብሔር ፍጥረቱን የሚመግብ አባት፣ በዕረፍት ውኃ ዘንድ የሚመራ/የሚያሰማራ እውነተኛ እረኛ መሆኑን የሚገልጹ ናቸው። (መዝ. ፳፪፥፩)

ስለዚህም የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ፍጥረትን በምሥጢርና በተለየ መንገድ እንድንመለከት ይመሩናል። ማለትም ዝናብ ውሃ ብቻ አይደለም፤ የእግዚአብሔር መግቦት ማስታወሻ ነው። ሰንበት ቀን ብቻ አይደለም፤ እሱ ምሥጢራዊ ዕረፍት ነው። ረሀብ የበረከት መራቅ ብቻ አይደለም፤ የእግዚአብሔር ምሕረት የሚገለጥበት ነው። ድህነት ማጣት ብቻ አይደለም፤ እሱ ከእግዚአብሔር ጸጋ መራቆትን የሚያሳይ ነው። የዝናቡ ኮቴ ድምፅ ብቻ አይደለም፤ እሱ እግዚአብሔር ምድርን እንዳልተዋት ማብሠሪያ ነው።

ስለዚህ ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ልብ ሁሉ እንዲህ ይበል፦ እግዚአብሔር ቅርብ ነው። የዝናብ ድምፅ የእግዚአብሔርን መቅረብ፣ ምሕረት እና ለፍጥረቱ የሚያደርገውን ቸርነት የሚያስታውሰን ከሆነ፥ ጥልቅ የሆነ ጥያቄ መጠየቅ አለብን፦ እግዚአብሔር በምድር ላይ የሰደደው ከሁሉ የሚበልጠው ዝናብ ነፋሳት ያልታከሉበት፣ ነጎድጓድ ያልተቀላቀለበት ዝናብ ምንድን ነው? አምላክ ወልደ አምላክ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ነው።

## 1.2. ዝናብ ክርስቶስ

ዝናብ በበጋ ድርቅ ሕይወት ያጡ ሰብሎች ነፍስ ለመዝራት ከሰማይ እንደሚወርድ ሁሉ፥ ክርስቶስም ለሞተው ዓለም ሕይወትን ለመስጠት ከሰማይ ወረደ።

ነቢያት ዝናብን የእግዚአብሔር የማዳን ጉብኝት ምልክት አድርገው የተጠቀሙበት ምክንያት ዝናብ ከላይ ስለሚመጣ፣ ሕይወትን ስለሚሰጥ፣ የደረቀውን ስለሚያለመልም እና ሰብልን ለፍሬ ስለሚያበቃ ነው። በተመሳሳይ መንገድ ክርስቶስ ከሰማይ መጣ፣ የሰውን ልጅ አደሰ፣ የጽድቅንና የዘላለም ሕይወትንም ፍሬ እንዲያፈራ አደረገ። መዝሙረኛው ስለ እርሱ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ፦ "እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ፥ በምድርም ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል።" (መዝ. ፸፩፥፮) ዓለም በኃጢአት ምክንያት ከመንፈስ ጽድቅ ምድረ በዳ ሆና ነበር፤ ነገር ግን ክርስቶስ እሷን ሕያው ለማድረግ ዝናብ ክርስቶስ መጣ።

ዝናብ ከሰማይ በሚወርድበት ጊዜ፥ ምድር የተራቡትን የሚያጠግብ ምግበ ሥጋን ታዘጋጃለች። እውነተኛ ዝናብ ክርስቶስም በሓጢአት የደረቀ ምድረ በዳ የሰውን ልጅ ወደሕይወት አምጥቷል። ትምህርቶቹና ምሳሌዎቹ የደረቁ ልቦችን አራሱ፤ የተጠሙ ነፍሳትን አረኩ፤ እምነትን፣ ንስሐን፣ ተስፋን እና ፍቅርን አበቀሉ።

"ዝናብ ከሰማይ እንደሚወርድ፥ ምድርን እንደሚያረካት፥ ታበቅልና ታፈራም ዘንድ እንደሚያደርጋት፥ ዘርንም ለሚዘራ እንጀራንም ለሚበላ እንደሚሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ፥ ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል።" (ኢሳ. ፶፭፥፲-፲፩) እውነተኛ ዝናብ አካላዊ ቃል ክርስቶስ "ፈልፈለ ማየ ሕይወት ዘይውሕዝ እምከርሱ፤ የሕይወት ውኃ ከእርሱ የሚፈልቅ" የተባለለት እርሱ መጣና ዓለምን በዝናም ወንጌል አጠጣት። (ዮሐ. ፩ ፥፩)

ክርስቶስ ለደረቀችና ለሞተችው ዓለም ሕይወትን ለመስጠት የወረደ ሰማያዊ ዝናብ ከሆነ፥ ይህ ሰማያዊ ዝናብ የመጣው ከየትኛው ደመና ነው? ዝናብ ያለ ደመና አይታይም፤ በማዳንም ምሥጢር ውስጥ፥ እግዚአብሔር የሕይወት ዝናብ በምድር ላይ በእሷ በኩል እንዲወርድ ቅድስትና ሕያው የሆነች ደመናን አዘጋጅቷል። ስለዚህ፥ የዝናቡን ምሥጢር ለመረዳት፥ አሁን የደመናዋን ምስጢር እናያለን።

## 1.2.1.ዝናም ክርስቶስን ለማስገኘት የታየች እውነተኛ ደመና ቅድስት ድንግል ማርያም

ከመጀመሪያው ጀምሮ፥ የሰው ልጅ አስከፊ ድርቅን አስተናግዷል፤ ይኸውም የውሃ ድርቅ ሳይሆን የጸጋ ማጣት ነው። በሔዋን አለመታዘዝ ምክንያት፥ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ረሃብና ጥማት ደረሰበት። በዓለም "ምልዓተ ኃጢአት" ሆኖ "ሁሉ በደለ" እንዲል የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ኅብረትም ተቋረጠ። የሕይወት ዛፍ ያለበት የገነት መንገድ ተዘጋ። የሰው ልጅ ከሕይወት እንጀራና መጠጥ ከሆነው ከእግዚአብሔር ተለይቶ ቀረ።

እግዚአብሔር ወደ እርሱ መጣ፤ ፈራጅ ብቻ ሆኖ አልመጣም፤ ተስፋ ጭምር ይዞለት መጣ። አዳም በተሸሸገበት እግዚአብሔር በሰኰና ብእሲ ድምፅ እያሰማው መምጣቱ የሰው ልጅን እንዳልተወው የመጀመሪያው ማብሠሪያ ነበር። ፍርድ ተነገረ፤ ነገር ግን ተስፋም አብሮ ተሰጠ። እግዚአብሔር የሴቲቱ ዘር ወልደ እግዚብሔር ክርስቶስ አንድ ቀን የእባቡን እራስ እንደሚቀጠቅጥ አስታወቀ። (ዘፍ. ፫፥፲፭)

ዝናብ በደመና በኩል እንደሚወርድ ሁሉ፥ ክርስቶስም ወደ ዓለም በድንግል ማርያም በኩል መጣ። በዚህም ምክንያት፥ "አማናዊት ደመና" ተብላ ትጠራለች፤ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም "አንቲ ዘበአማን ደመና እንተ አስተርአይኪ ለነ ማየ ዝናም፤ የዝናብ ውሃ የታየብሽ እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ።" እንዲል፤ ዝናብ ክርስቶስን

ለዓለም ያስገኘች ብርህት ደመና ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ነቢዩ ኢሳይያስ "እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ላይ ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል" (ኢሳ. ፲፱፥፩) ሲል ትንቢት ተናገረ። "ፈጣን ደመና" የተባለችው ኃጢአት የሌለባት፣ ንጽሕተ ንጹሐን የሆነችው እመቤታችን ናት።

በ፩ኛ ነገሥት ምዕራፍ ፲፰ ላይ ምድሪቱ በድርቅ በምትሰቃይበት ወቅት፣ ነቢዩ ኤልያስ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ ጫፍ ወጥቶ በጸለየ ጊዜ የታየችው ያች የሰው እጅ የምታክል ታናሽ ደመና ወዲያውኑ ሰማዩን አጨልማ ታላቅ ዝናብ እንዳዘነበችና ምድርን ከሦስት ዓመት ከስድስት ወር ድርቅ እንዳሳረፈች ሁሉ፣ ድንግል ማርያምም ትሑት ሆና ሳለች (ሉቃ. ፩፥፵፰) ከባሕር (ከደቂቀ አዳም) ተለይታ በቅድስና የወጣች (ከፍ ያለች) አማናዊት ደመና ለሰው ልጆች ሁሉ የበረከት ዝናብ የሆነውንና መላውን ዓለም ከዘለዓለም የነፍስ ድርቅ የታደገውን ክርስቶስን አስገኘች።

ደመና ምድራዊ ዝናብን ይሸከማል። እመቤታችን ማርያም አማናዊ ዝናብ ክርስቶስን ተሸከመች። ደመና አዝርዕትን የሚያጠጣ ዝናም ያስገኛል። ማርያም ነፍሳትን የሚያጠጣውን እርሱን ወለደች። ደመና ለሰብሎች ሕይወትን የሚሰጥ ዝናብ ለማዝነብ ይታያል። ማርያም ለአዝርዕት ምእመናን የዘለዓለም ሕይወትን የሚሰጠውን ክርስቶስን ለማስገኘት ታየች።

ስለዚህ፥ ድንግል ማርያም ዝናብ ክርስቶስ የተገኘባት እውነተኛ ደመና ሆና በማዳን ታሪክ ውስጥ ትልቅ ሚናን ተወጥታለች።

የድኅነት ታሪክ የሚጀምረው በሴት ነው። በኤደን ገነት፣ ሔዋን በሰው ልጅ አሳዛኝ ታሪክ መግቢያ ላይ ቆማ ነበር። "ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ... ባየች ጊዜ ከፍሬው ወሰደችና በላች፤" እንዲል። (ዘፍ. ፫፥፮) ቅዱስ ኤፍሬም "ስለሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ፤

ስለድንግል ማርያም ተከፈተልን፤ ዳግመኛ ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን" እንዲል፤ እግዚአብሔር በሔዋን ውድቀት ምክንያት ሴትን አላገለለም፤ ዳግሚት ሔዋን ድንግል ማርያም ከማሕፀንዋ እንድትወለድ ያውቃልና:: ይኸውም ከውድቀት በኋላ ወዲያውኑ፣ የሚመጣው ድል ወይም ትንሣኤ ከሴት ጋር የተያያዘ እንደሚሆን አወጀ:: "በአንተና በሴቲቱ፣ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ::" (ዘፍ. ፫፥፲፭)

የመጀመሪያው የቤዛነት ትንቢት የተነገረው ስለ ሴቲቱ ዘር ነው:: ስለዚህ፣ ከመጀመሪያው አንስቶ ሴት የችግሩ አካል ብቻ አልነበረችም፤ በእግዚአብሔር የማዳን ዕቅድ ውስጥ ተካታ ነበር:: ከዘመናት በኋላ፣ ድንግል ማርያም የዚህ ተስፋ ፍጻሜ ሆነች:: "እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥" (ኢሳ. ፯፥፲፬) ድኅነት በድንግል ማርያም በኩል ብቻ እንደሆነ (እግዚአብሔር ነጸረ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ውስተ ኵሉ አጽናፍ ወኢረከበ ዘከማኪ ፈነወ ዋሕዶ ወተሰብአ እምኔኪ፤ እግዚአብሔር ከሰማይ ሆኖ ምሥራቅና ምዕራብ ሰሜንና ደቡብ ዳርቻዎቹ ሁሉ አየ እንደ አንቺ ያለ ሰው አላገኘም፤ አንድያ ልጁን ወደ አንቺ ላከ" ብሎ በድኅነተ ዓለም ያላት ድርሻ ይናገራል::

በማርያም በኩል፣ ሰማያዊው ዝናብ እራሱ ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ:: ይህ ለኦርቶዶክሳውያን ሴቶች ጥልቅ የሆነ እውነትን ይገልጣል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በድኅነት ታሪክ ውስጥ በሴት በኩል ትልቅ ሥራ ሠርቷል::

### 1.2.2. ዝናም ወንጌልን ለማዝነም የተላኩ ሐዋርያት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ሰማይም በዓረገ ጊዜ፥ ዓለምን ያለ ዝናብ ወንጌል አልተዋትም:: ይልቁንም ወንጌሉን ለሐዋርያት አደራ ሰጣቸው፣ ወደ ዓለም ሁሉ ላካቸው፤

እንዲህም ሲል አዘዛቸው፤ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. ፳፰፥፲፱) ይህ የሚያሳየን ዝናብ ወንጌልን ለአዝርዕት ምእመናን ከይብሰት ኃጢአትና ክህደት ይታደጋቸው ዘንድ መድረስ እንዳለበት ነው።

"ደመናት ድምፅን ሰጡ" (መዝ. ፸፯፥፲) እንዲል ሐዋርያትም የሕይወትን ዝናብ የክርስቶስ ቃል የተሸከሙ መንፈሳዊ ደመናት ሆኑ። ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ደመናት ውስጥ ቅዱሳን ሐዋርያትንና የወንጌል ሰባኪዎችን በተደጋጋሚ አይታለች። በተጓዙበት ስፍራ ሁሉ የክርስቶስን ዝናም ወንጌልን አዘነቡ። ዝናብ ወንጌልን በአይሁድና በአሕዛብ፣ በባለጠጎችና በድሆች፣ በገዥዎችና በአገልጋዮች፣ በወንዶችና በሴቶች ላይ ሁሉ በእኩልነት አፈሰሱ። አምልኮ ጣዖት ነፍስን ባደረቀበት ስፍራ፥ እነሱ ዝናብ ቃለ እግዚአብሔር አዘነቡ። ኃጢአት ልቡና ሰብእ ባደረቀበት ስፍራ፥ ዝናብ ንስሓን አመጡ። ምድረ በዳ ተስፋ ቢስነት በተፈጠረበት ዝናብ ተስፋ አዘነቡ።

ቅዱስ ጳውሎስ "እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር" (፩ኛ ቆሮ. ፫ ፥፮) እንዲል በሀይማኖት እርሻ ተክል አማኝ ተክለው በወንጌል ዝናም የሚያበቅሉና የሚያሳድጉ እንዲሁም ለፍሬ ምግባር ያደረሱት ሐዋርያት ናቸው።

መንግሥተ ሰማይ ተስፋ፣ ተስፋ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ክርስቶስ ወንጌል ብለው መተርጕማኑ እንደገለጹት ዝናብ ክርስቶስ፣ ክርስቶስ ወንጌል፤ ዝናም ወንጌልን ለዓለም ያዘነቡት ሐዋርያት በድኅነተ ዓለም ሱታፌ አላቸው።

## 1.2.2.1.አርድእት፣ ሐዋርያውያን አበው፣ ሊቃውንትና መምህራን ሐዋርያት ባዘነቡት ዝናብ ወንጌል አማካኝነት የበቀሉ ቡቃያዎች

ዝናብ በለመለመ መሬት ላይ በሚወርድበት ጊዜ ምድርን ሳይለውጣት አይተዋትም:: አዝርዕት ይበቅላሉ፤ ማደግ ይጀምራሉ፤ ሥሮችም በመሬቱ ውስጥ በጥልቀት ይስፋፋሉ፤ ፍሬም ያፈራሉ፤ መከር ላይም ያማረ ፍሬያቸው በጎተራ ይሰበሰባል:: በተመሳሳይ መንገድ፥ ሐዋርያት ዝናብ ወንጌልን በዓለም ላይ ባዘነቡ ጊዜ፥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው መንፈሳዊ ቡቃያ ምእመናን በቀሉ::

ሐዋርያት አማኞችን ብቻ አላፈሩም፤ እነርሱን መስለው እነርሱን አህለው የሚታዩ ደቀ መዛሙርትን አፈሩ እንጂ:: ለቀጣዩ ትውልድ የክርስቶስን ሥራ እንዲቀጥል አዘጋጁ:: ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ልጁን ጢሞቴዎስን እንዲህ ሲል አዝዞታል፤ “በብዙ ምስክሮች ፊት ከእኔ የሰማኸውንም ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ” (፪ኛ ጢሞ. ፪፥፪) እንዲል::

ክርስቶስ ሐዋርያትን አስተማረ፤ ሐዋርያት ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስተማሩ፤ ሐዋርያነ አበው ሊቃውንትን አስተማሩ:: ሊቃውንት መምህራንን አስተማሩ:: በዚህ የትውልድ ቅብብሎሽ፣ ትውፊት ሀይማኖታችን እስከ አለንበት ዘመን ደረሰ:: አንድ የዝናብ ወራት በሺዎች የሚቆጠሩ ዕፅዋትን ማብቀል እንደሚችል ሁሉ፥ የሐዋርያት ስብከትም በታሪክ ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን የእግዚአብሔር አገልጋዮች አፈራ:: የፈሉት ችግኞች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፥ ሕይወቱ ግን አንድ ነው:: ሠራተኞቹ ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፥ ጌታው ግን አንድ ነው:: መምህራኑ ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፥ እውነቱ ግን አንድ ነው:: የክርስቶስ ወንጌል አይቀየርም::

ቤተ ክርስቲያን ሰፊ መንፈሳዊ የአትክልት ስፍራ ነው። ወንጌል ዝናብ ነው። እግዚአብሔር የአትክልት ቦታውን ይንከባከባል። ነቢዩ ኢሳይያስ "እግዚአብሔርም ዘወትር ይመራሃል... አንተም እንደሚጠጣ የገነት/ የአትክልት ስፍራ ትሆናለህ" (ኢሳ. ፶፰ ፥፲፩) ይላል።

ዛሬም ቢሆን፥ እያንዳንዱ ታማኝ መምህር፣ ሰባኪ፣ አገልጋይ እና መንፈሳዊ መሪ በዚህ ሰፊ ሁዳድ ላይ ይቆማል። የሐዋርያት ሀይማኖት በታማኝነት ሲዳረስ አዳዲስ ቡቃያዎች ይወጣሉ፥ አዳዲስ ፍሬዎች ይታያሉ። ወንጌል ዝናብ በሐዋርያት አልቆመም፤ ዝናብ ወንጌል መቼም አያባራም፤ ካቆመ ሕይወት ያቆማልና፤ ክርስቶስ አሁንም ቤተ ክርስቲያኑን ያጠጣታል። "ትውልድ የኃልፍ ትውልድ ይተርፍ፤ ትውልድ ያልፋል፤ ትውልድ ይተርፋል" ነውና እግዚአብሔር ሁልጊዜ ሰው ያስነሣል።

### 1.2.2.1.1. እስከ ምጽአት ድረስ በሚዘንመው ዝናም ወንጌል ዘመኑን የዋጁ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ሚና

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን እንዲህ ሲል አዟቸዋል፤ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር. ፲፮፥፲፭) ይህ ትእዛዝ ለመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ብቻ የተሰጠ አልነበረም። እሱ እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ የቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ሆኖ ይኖራል።

ዛሬ ይህ አደራ ከተሰጣቸው መካከል በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በቤተ ክርስቲያን በግቢ ጉባኤ ውስጥ የሚሰበሰቡት ወጣቶች ይገኛሉ። እነዚህ ተማሪዎች ልዩ በሆነ የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ ይኖራሉ። አብዛኛው ጊዜያቸው ምድራዊ ትምህርት በመቅሰም ያሳልፋሉ። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወትን ለመማር በቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ። ይህ ጥሪያቸው ልዩ ዕድል ያደርገዋል። ሐዋርያት ከመላካቸው በፊት እንደተማሩ ሁሉ፥ እነዚህም ተማሪዎች በቤተ ክርስቲያንና በማኅበረሰቡ ውስጥ ትልቅ አደራ ተቀብለው ሊላኩ እየሠለጠኑ ነው።

ግቢ ጉባኤ ቡቃያዎች በዓለም ሰፊ እርሻ ከመተከላቸው በፊት የሚኮተኮቱበት እንደ መንፈሳዊ የችግኝ ጣቢያ ነው፡፡ ይህ ስፍራ የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ከትንሽ ኃላፊነት እስከትልቁ ፕትርክና ድረስ የሚይዙ ታላላቅ ምሁራን የእምነት አርበኞች የሚዘጋጁበት ጣቢያ ነው፡፡

ዝናብ ወንጌል በእነሱ ላይ የሚወርደው በቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች፣ በሥርዓተ አምልኮ ሕይወት፣ በመንፈሳዊ አባት እና ከምእመናን ጋር በሚደረግ ኅብረት በኩል ነው፡፡ ዝናብ ዘንቦለት የማያበቅል እርሻ የተፈጥሮ ግዴታውን አልተወጣም፡፡ መንፈሳዊ ምግብን የሚቀበሉ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎችም ሌሎችን የሚጠበቅባቸው የቤተክርስቲያን ኃላፊነት ለመሸከም መዘጋጀት አለባቸው፡፡

ይህ ኃላፊነት በተለየ ሁኔታ አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም የዩኒቨርሲቲ አካባቢዎችና ከወጡም በኋላ ያሉበት ዓለም ተማሪዎችን ለተለያዩ ተፎካካሪ ሐሳቦች፣ ፍልስፍናዎች፣ ፈተናዎች እና የእምነት ተግዳሮቶች የሚያጋልጡ ስለሆኑ ማለት ነው፡፡ ለጥርጣሬ፣ ለቁሰኝነት (ማቴሪያሊዝም)፣ ለሥነ-ምግባር መታወክ፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ግድየለሽ መሆን የሚጋበዙ ሁሉ እንዲቋቋሙ ትጋት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ታማኝ የክርስቶስ ምስክሮች እንዲሆኑ ተጠርተዋልና፡፡ በትዕቢት፣ ለክርክር በሚደረግ ሙግትም አይደለም፡፡ ነገር ግን በመልካም ጠባይ፣ በትክክለኛ ዕውቀት፣ በትሕትና፣ በጥበብና በፍቅር ነው እንጂ፡፡ ሐዋርያው "በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን" (፩ ጴጥ. ፫፥፲) እንዲል፡፡

ስለሆነም፥ የቤተ ክርስቲያን ተማሪዎች ኅብረት አባላት ጥሪያቸውን ከቶ ማቃለል የለባቸውም፡፡ እነሱ በእግዚአብሔር የወይን ቦታ ውስጥ የተኮተኮቱ ናቸው፡፡ እነሱ ከክርስቶስ በሐዋርያት፣ በአባቶች፣ በመምህራንና አገልጋዮች በኩል በሚዘንም ዝናብ ወንጌል የተገኙ

ናቸውና። ታማኝ ሆነው በመቀጠል፥ እነሱ ራሳቸው ያው ሕይወት ሰጪ የሆነውን ዝናብ ወንጌልን እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ለሚመጡት ትውልድ የሚደርስበት መሣሪያ መሆን ይገባቸዋል።

### 1.2.2.2. በዝናም ወንጌል የበቀሉ ቡቃያዎች ቅዱሳን ሴቶች

ወንጌል ሴቶች በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ፣ የዘለዓለምን ሕይወት ለመውረስ እንደተጠሩ እውነተኛ ክብራቸው ገለጠ። በምድራዊ አገልግሎቱ ሁሉ ጌታችን ለሴቶች እንክብካቤና ክብርን አሳይቷል፤ እነሱም ተከተሉት፤ አገለገሉት፤ ትምህርቱንም አዳመጡ። ስለዚህም ሌሎች ብዙዎች በሸሹ ጊዜ በመስቀሉ አጠገብ በታማኝነት የቆሙ ሴቶች አሉ። በትንሣኤውም የመጀመሪያ ምስክሮች ነበሩ።

ከመቶ ሃያ ቤተሰብ መካከል ክርስቶስን አብረውት የተከተሉና አገልግሎቱን የደገፉ ሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ናቸው። እንደ መግደላዊት ማርያም፣ ዮሐና፣ ሶስና፣ የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም፣ እና ሰሎሜ ያሉ ቅዱሳት አንስትን በመጽሐፍ ቅዱስ ስማቸው በግልጥ ይጠቀሳሉ።

ልክ እንደ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት የወንጌልን ዝናብ ወደ ዓለም ሁሉ በተሸከሙ ጊዜ የሚራዷቸው ሴቶችን መረጡ።

ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ሳይክዱ ስደትንና መከራን የተቀበሉትን ቅዱሳት አንስት በክብር ታስባቸዋለች። እነሱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሀብት፣ ከምቾት፣ ከዝና ወይም ከእራሳቸው ሕይወት አስበልጠው ወደዋልና። አንዱን የጋራ የሕይወት ምንጭ ክርስቶስን ተጋርተዋልና።

#### 1.2.2.2.1. እስከ ምጽአት ድረስ በሚዘንመው ዝናም ወንጌል ዘመኑን የዋጁ የግቢ ጉባኤ ሴቶች ልዩ ድርሻ

በሐዋርያት አማካኝነት የዘነበው የወንጌል ዝናብ በአንድ ዘመን የነበሩትን ቅዱሳንን ማፍራት ብቻ አልነበረም፤ በየዘመናቱ ታማኝ

ሴቶችን ማፍራቱን ይቀጥላል እንጂ፡፡ ከዚህ ሰማያዊ ዝናብ ፍሬዎች መካከል ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት በቤተክርስቲያን ኅብረት ውስጥ ያደጉና የታነጹ የግቢ ጉባኤ ሴት ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡ ያሉበትን ግቢ ጉባኤ ትተው ወደ ሰፊው የአገልግሎት መስክ ሲገቡ በእምነት፣ በትምህርት፣ በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያን እና በኅብረተሰብ መካከል ባለው ወሳኝ ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ፡፡

ሴቶች ሚናቸውን ለመረዳት ጥንት ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ ደጋግ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ያበረከቱ ብዙ ሴቶች ሲኖሩ የተወሰኑት እንመልከት፡፡

- ሐና፡- ሳሙኤል ነቢይ ከመሆኑ በፊት፣ ሐና ነበረች፡፡ “ስለዚህ ብላቴና ጸለይሁ፤ እግዚአብሔርም የለመንሁትን ልመናዬን ሰጥቶኛል፤” (፩ኛ ሳሙ. ፩፥፳፯) እንዲል፡፡
- ዮካብድ፡- ሙሴ ሕዝበ እስራኤልን ከፈርዖን እጅ ከማዳኑ በፊት፣ ዮካብድ ነበረች፡፡ “ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ... በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት፡፡” (ዕብ. ፲፩፥፳፫) የእናቱ ድፍረት እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያድንበትን ሰው ታድጓል፡፡ በኋላም ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሕጉ ስለ ማንነቱ እየነገረች አሳድጋዋለች፡፡
- ኤውንቄና ሎይድ፡- ጢሞቴዎስ ኤጲስ ቆጶስና የምእመናን እረኛ ከመሆኑ በፊት፣ ኤውንቄና ሎይድ ነበሩ፡፡ “በአንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አስባለሁ፤ ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው” (፪ኛ ጢሞ. ፩፥፭) ብሎ ጳውሎስ እንደተናገረው የሁለት ሴቶች እምነት የወደፊቱ የቤተክርስቲያን መሪ መገኛ ሆነ፡፡

እነዚህ ምሳሌዎች አንድን ሥርዓት ይገልጣሉ፤ ወንዶች ብዙ ጊዜ በታሪክ ውስጥ በአደባባይ ይታያሉ፡፡ ሴቶች ደግሞ ብዙ ጊዜ ታሪክ ከመታየቱ በፊት ይቀርጹታል፡፡

ለግቢ ጉባኤ ሴት ተማሪዎች ወይም ተመራቂዎች ይህ ወሳኝ ትምህርት ነው፡፡ ዲግሪዎች በሮችን ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡ ክሂሎቶች እድሎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ግን ዘላቂ ፍሬያማነት ያመጣል፡፡

መጽሐፈ ምሳሌ ጠቢብ ወይም ልባም ሴት "አፍዋን በጥበብ ትከፍታለች፤ የርኅራኄም ሕግ በምላስዋ አለ፡፡" እያለ ተጽዕኖዋ ከእርሷ አልፎ የሚዘልቅ መሆኑን ይገልጻል፡፡ (ምሳሌ ፴፩፥፳፮)

የእሷ ተጽዕኖ በቤተሰቧ፣ በማኅበረሰቧ እና በመጪው ትውልድ ላይ ይደርሳል፡፡ ይህ መርሕ ሴቶች በተሰማሩበት ዘርፍ በመምህርነት፣ የጤና ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ ተመራማሪዎች ሆነው የወንጌል አገልግሎትን ይሰጣሉ፡፡

በዚህ ልክ ኀላፊነታቸው ከተወጡ ሐዋርያው እንደተናገረው ከንቱ የአሮጊት ተረት የሆነ በዘመናችን የበቀለ "ዘመን የወለደው ንጉሥ የወደደው" እንዲሉ አበው ለሴቶች የተቆረቆሩ መስለው "ቅቤ አንጓቾች" ፌሚኒስት የሚባሉት እውነተኛ የሆነውን የቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮ በመጻረር ብቅ ያሉትን ስሑት እሳቤያቸውን ማፍረስ ይችላሉ፡፡

"ወንድ ወይም ሴት የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡" (ገላ. ፫፥፳፰) ይህ አንድ መሆን የሰዎችን ልዩ ስጦታዎች የሚያጠፋ አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በእግዚአብሔር ጥበብ ውስጥ የተለያዩ ጥሪዎችን እየፈጸሙ፣ በእርሱ ፊት እኩል ክብር እንደሚቀበሉ ያስተምራል፡፡ አንዱ የሚወጣውን ድርሻ ሌላው አካል ላይወጣው ይችላል፡፡

ስለሥልጣን እንኳ ብንነጋገር ክርስትና ስለ ሰው ልጅ ዋጋና ክብር ሲሰጥ በሥልጣን፣ በውድድር ወይም የበላይነትን ለማግኘት በሚደረግ ትግል አይጀምርም፡፡ እሱ የሚጀምረው በእግዚአብሔር አምሳል

በመፈጠርና ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረገው ኅብረት ባለው ግንኙነት ውስጥ ነው። የወንጌል ዓላማ የአንድ ጾታ በሌላው ጾታ ላይ ድል መቀዳጀት አይደለም። ዓላማው ወንዶችንም ሴቶችንም ክርስቶስን ወደ መምሰል መለወጥ ነው። ስለሆነም የክርስቲያን ጥያቄ "እንዴት የበለጠ ሥልጣን ማግኘት እችላለሁ?" የሚል ሳይሆን፥ "እንዴት ክርስቶስን መምሰል እችላለሁ?" የሚል ነው።

በፌሚኒዝም አራማጆች ዘንድ ነጻነት ከማንኛውም ሥልጣን፣ ከማንኛውም ባህላዊ እሴት (ትውፊት) ወይም በወንዶችና በሴቶች መካከል ካለው ልዩነት ሁሉ ነጻ መሆን ተደርጎ ይተረጎማል። ወንጌል ግን ከዚህ የተለየ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ "አሁን ግን ከኃጢአት አርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘለዓለም ሕይወት ነው።" (ሮሜ ፮፥፳፪) እንዲል፤ ነጻነት ማለት ከኃጢአት አርነት መውጣት ነው። እውነተኛ ክብር

**በቅዱስ ቊርባን አማካኝነት ክርስቶስ ሕያው ያደረጋቸውን ነፍሳት መመገቡን ይቀጥላል ። የደረቀችና የተራበች ነፍስ ምግብን ታገኛለች ። የደከመች ነፍስ ጥንካሬን ታገኛለች ። የቆሰለች ነፍስ ፈውስን ታገኛለች ። የዛለች ነፍስ መታደስን ታገኛለች ።**

የሚገኘው በቅድስና ውስጥ ነው:: እውነተኛ ታላቅነት የሚገኘው ትሕትና ባለው አገልግሎት ውስጥ ነው:: እውነተኛ ጥንካሬ የሚገኘው ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ውስጥ ነው:: ይህም ለወንዶችም ለሴቶችም ነው::

በክርስትና ታሪክ ውስጥ ታላቋ ሴት ድንግል ማርያም የሰው ልጅን ታሪክ አቅጣጫ የለወጠችው በፖለቲካ ሥልጣን፣ በሀብት ወይም በማኅበራዊ ተጽዕኖ ሳይሆን በእምነት፣ በንጽሕና፣ በትሕትና እና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ነው:: የእሷ ቃል "እነሆኝ የጌታ ባሪያ" (ሉቃ. ፩ ፥፴፰) የሚል ነበር:: ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ከእሷ በላይ የከበረች ሴት አይደለም የከበረ ምንም ዓይነት ፍጡር የለም:: ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ትሑት መሆን ደካማነት አይደለም፤ እሱ ወደ ታላቅነት የሚወስድ ረቂቅ መንገድ ነው እንጂ::

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ በሴት አንቀጽ ቅድስት ሥላሴ፣ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ብላ ትጠራለች፤ እንዲሁም ሥላሴ ፈጠረኝ ብለን በወንድ አንቀጽ እንጠራለን:: እስከዚህም ቢመራመሩ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንዲት ነቀፌታ አያገኙባትም::

የግቢ ጉባኤ ሴት ተመራቂዎች ለዓለም የተለየ ምስክርነትን ለማቅረብ ልዩ ስፍራ አላቸው:: የተሰጣቸውን ክብርና ኀላፊነት በመወጣት ማረጋገጥ ይችላሉ:: መንፈሳዊ ማንነታቸውን ሳያጡ ትምህርታቸውን መከታተል ይችላሉ:: የሥነ-ምግባር ንጽሕናቸውን ዕሴታቸውን ሳያጡ በሙያቸው የላቀ ደረጃ ላይ መድረስ ይችላሉ:: ለክርስቶስ ትምህርት ታማኝ ሆነው ሳሉ ስለ ፍትሕ መሟገት ይችላሉ::

በአገልግሎት የድርሻችሁን ተወጥታችሁ ዘመኑን በዋጀ መልኩ "የእኛ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ናት" ብላችሁ ዐቃቤ እምነት (Apologetic) ሆናችሁ መገኘት ይጠበቅባችኋል::

ስትመረቁና ወደ ቀጣዩ የሕይወት ምዕራፍ ስትሸጋገሩ፣ ትልቁ ስኬታችሁ የምትቀበሉት ዲግሪ/ዲፕሎማ... ሳይሆን የምታዳብሩት ሥነ-ምግባር (ጸባይ) መሆኑን አስታውሱ::

- ዓለም ሙያችሁን ሊያስታውስ ይችላል፤ እግዚአብሔር ግን ታማኝነታችሁን ያስታውሳል።
- ዓለም ስኬታችሁን ሊያከብር ይችላል፤ መንፈሳዊው ዓለም ግን በቅድስናችሁ ሐሴት ያደርጋል።
- ዓለም ምን ያህል ሥጋዊ ነገር እንዳተረፋችሁ ሊጠይቅ ይችላል፤ ክርስቶስ ግን ምን ያህል ፍሬ እንዳፈራችሁ ይጠይቃል።

በጸሎት፣ በንጽሕና፣ በአገልግሎት፣ በፍቅር፣ በእምነት ጽኑ። የሳራን እምነት፣ የሐናን ጸሎት፣ የዮካብድን ድፍረት፣ የኤውንቄን ትምህርት፣ የድንግል ማርያምን መታዘዝ እና የየዘመናቱን ቅዱሳት አንስት ያፈራው ያው ዝናብ ቃለ እግዚአብሔር ዛሬም እየዘነበ ነውና።

ያ ሰማያዊ ዝናብ ሕይወታችሁን ፍሬያማ ማድረጉን ይቀጥል፤ ከዚያም ቀጥሎ በምስክርነታችሁ፣ በአገልግሎታችሁ፣ በጥበባችሁ፣ በወደፊቱ ቤተሰባችሁ፣ በተልዕኳችሁ ሁሉና በታማኝነታችሁ በኩል፣ እስከ ዕለተ ሞታችሁ ብዙዎች ክርስቶስን እንዲያውቁ ማድረግ ይኖርባችኋል።

### 1.2.3. በዝናም ክርስቶስ ከይብሰት ሲኦል ወደ ልማላሜ ገነት የተሸጋገረች ነፍስ

የክርስቶስ ቤዛነት በምድር ላይ በሕይወት ባሉ ሰዎች "ድውያነ ነፍስን በትምህርት ድውያነ ሥጋን በተአምራት" አድኖ ያበቃ ሳይሆን በመስቀል ተሰቅሎ በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል ወርዶ "ሰበከ ሎሙ ግዕዛነ፤ ነጻነትን ሰበከላቸው" ቅዱስ ጴጥሮስ "ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው" (፩ኛ ጴጥ. ፫፥፲፱) እንዲል፤ ዝናም የክርስቶስ ምሕረት እስከሲዖል ወረደ። በነፍስ ጥም የተቃጠለ ነፍስ በአንዴ ረካ፤ "እለውስተ ሲዖል ጻኡ ወእለ ውስተ ጽልመት ተከሰቱ፤ ከሲዖል ያላችሁ ውጥ በጨለማ ያላችሁ ተገለጡ" ብሎ ከሞት ወደሕይወት

አሸጋገራቸው:: ይብሰት ሞት አጥፍቶ ልምላሜ ሕይወት ሰጣቸው:: ከበረሀ ሲያል አላቆ የአትክልት ሀገር ደጋ ገነት አደረሳቸው:: ሕይወት ክርስቶስ ወደ ሞት ግዛት ገባ:: ዝናብ ክርስቶስ ወደ ደረቁ ምድር ወረደ:: ይብሰት ሲኦል በዝናም ክርስቶስ ተሸንፎ ስፍራውን ለልምላሜ ገነት ለቀቀ::

## 1.2.4. በዝናም ክርስቶስ ከይብሰተ ኃጢአት ወደ ልምላሜ ንስሐ፣ ቍርባንና ሥነ ምግባራት የተሸጋገሩ (የወጡ) ነፍሳት

ከወንጌል ታላላቅ ተአምራት አንዱ የሁኔታዎች መለወጥ ብቻ ሳይሆን የነፍሳት መታደስ (መለወጥ) ነው:: ዝናብ ከመዝነቡ በፊት ምድር ደረቅ ናት፤ ይሰነጠቃል፤ ስለዚህም ተክሎች ይጠወልጋሉ:: ሕይወት ለመኖር ትታገላለች:: በተመሳሳይ መንገድ፥ ነፍስ ከእግዚአብሔር ተለይታ ስትኖር መንፈሳዊ ድርቀት ይከሰታል:: እምነት ይደክማል:: ጸሎት ከባድ ይሆናል:: ፍቅር ይቀዘቅዛል:: ኅሊና ይደነዝዛል:: ኃጢአትም የበላይነትን ይይዛል::

"ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬም አንተን ናፈቀች፥ ውሃ በሌለበት በደረቅና በተጠማ ምድር::" (መዝ. ፷፫፥፩) ይህ ይብሰት ምድራዊ ንብረት በማጣት የሚመጣ አይደለም:: ብዙ ሰዎች ሀብት ኖሯቸው እንኳ አሁንም መንፈሳዊ ድርቀት አለባቸው:: ብዙዎች እውቀት አላቸው ነገር ግን አሁንም መንፈሳዊ ጥም አለባቸው:: ብዙዎች በዓለማዊ ተድላ ይደሰታሉ ሆኖም ውስጣቸው ድርቀት ይሰማቸዋል::

የሰው ነፍስ ጥሟን ሊረካ የሚችለው በእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው:: በዚህ ምክንያት ክርስቶስ ዝናብ መጣ:: እርሱም፦ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ" (ዮሐ. ፯ ፥፴፯) ሲል አወጀ:: እርሱ እራሱ የሕይወት ውኃ ምንጭ ነው "ፈልፈለ ማየ ሕይወት ዘይውሕዝ እምከርሱ፤ የሕይወት ውኃ ከእርሱ የሚፈልቅ" እንዲል ቅ. ያሬድ::

## ሀ) ከይብሰተ ኃጢአት ወደ ልምላሜ ንስሓ

ክርስቶስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ" (ማቴ.፬ ፥፲፯) እንዲል የመጀመሪያው በረከት ንስሓ ነው። ዝናብ የደረቀውን አፈር እንደሚያለሰልስ ሁሉ፥ የእግዚአብሔርም ጸጋ የደነደነውን ልብ ያለሰልሳል። ክፋትን ይወድ የነበረው ኃጢአተኛ ክፋቱን መጥላት ይጀምራል። ትዕቢተኛ ልብ ራሱን ማዋረድ ይጀምራል። ቸልተኛ ነፍስ እግዚአብሔርን መፈለግ ይጀምራል። የንስሓ ዕንባ መፍሰስ ይጀምራል። በሁኔታዎች ማመካኘት ትቶ በመናዘዝ ይተካል። ተስፋ መቁረጥም በተስፋ ይተካል።

## ለ) ከመንፈሳዊ ረኃብ ወደ ቅዱስ ቊርባን

ዝናብ መሬቱን ማለስለስ ብቻ ሳይሆን ምግብንም ያስገኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ክርስቶስ ኃጢአትን ይቅር ማለት ብቻ ሳይሆን፤ ነፍሳትንም ይመግባል። ጌታ እንዲህ ሲል እንደ አወጀው "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" (ዮሐ. ፮፥፴፭) ደግሞም፦ "የሰው ልጅን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በእራሳችሁ ሕይወት የላችሁም" (ዮሐ. ፮፥፶፫) እንዲል በቅዱስ ቊርባን አማካኝነት ክርስቶስ ሕያው ያደረጋቸውን ነፍሳት መመገቡን ይቀጥላል። የደረቀችና የተራበች ነፍስ ምግብን ታገኛለች። የደከመች ነፍስ ጥንካሬን ታገኛለች። የቆሰለች ነፍስ ፈውስን ታገኛለች። የዛለች ነፍስ መታደስን ታገኛለች።

## ሐ) ከፍሬ አልባነት ወደ ጣፋጭ ፍሬ ምግባር

ዝናብ ልምላሜን መፍጠር ብቻ ሳይሆን ጥቅሙ ሰብልን ፍሬ እንዲያፈራ ማድረግ ጭምር ነው። በተመሳሳይ መልኩ፥ የክርስቲያን ሕይወት በንስሓ ወይም በምሥጢራት በመሳተፍ ብቻ የሚያበቃ አይደለም። ግቡ በጎ ምግባራት ማድረግ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መንፈስ ፍሬዎች ይናገራል፦ “ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት” (ገላ. ፭፥፳፪-፳፫) አምላካችንም “ተርቤ አብልታችሁኛል፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛል፤ ታርዤ አልብሳችሁኛል፤ ታምሜ ጠይቃችሁኛል፤ ታስሬ ወደእኔ መጥታችኋል” (ማቴ. ፳፭፥፴፭) እንዳለ በጎ ምግባራት የክርስቶስ ዝናብ ወንጌል በነፍስ ውስጥ እየሠራ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው።

እንደአጠቃላይ ዝናብ ክርስቶስ ወርዶልን ከኃጢአት አድኖን ሕይወትን አደለን። ክርስቶስ የሾማቸው ሐዋርያት ደግሞ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ዝናም ወንጌል ለተማሪዎቻቸው ለሐዋርያነ አበው አስተላልፈዋል። ሐዋርያነ አበው ደግሞ ለሊቃውነት፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ለመምህራን እያሉ እስከዚህ ድረስ ዝናብ ወንጌል መዝነቡን ቀጥሏል፤ በረድ ክህደት ያልተቀላቀለበት ለሰብል የሚስማማ በዝቶ መሬቱን ሸርሽሮ የተክል ሥር የማይፈነቃቅል፣ አንሶ ሰብል እንዳይጠወልግ በመጠን አድርገው ዝናብ ወንጌል እስከ ዘመናችን እንዲዘንብ እንዳደረጉ እኛም በዝናቡ ተጠቅመን ለቀጣይ ትውልድ ማሸጋገር ይገባናል። አምላካችን “እስከ ዓለም ፍጻሜ ከእናንተ ጋር ነኝ።” እንዲል ትናንት ሐዋርያት፣ ሊቃውንት፣ መምህራን ያስነሣ አምላክ ዘሬም ነገም ያስነሣል። ከክብሩ እንድንሳተፍ “የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ” (፪ኛ ጢሞ. ፬፥፭) እንዲል በምንሰማራባቸው ልዩ ልዩ የሥራ መስኮች የወንጌል ሥራ መሥራት ይገባናል።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር አሜን።

# ዕውቀት፣ እምነትና መሪነት

## ክፍል ሁለት

በዝግጅት ክፍሉ

በጉባኤ ቃና ፲፰ኛ ዓመት ቁጥር ፩ ግንቦት ፳፻፲፰ ዓ.ም ባወጣነው መጽሔት ላይ፣ በጉባኤ ቃና ቁጥር ፪ እንደሚቀጥል ያሳወቅናችሁ "ዕውቀት፣ እምነትና መሪነት" በሚል ርእስ ያሰናዳነው የዶክተር ወርቁ የሕይወት ተሞክሮን ልናስነብባችሁ ወደናል።

በቁጥር አንድ ጉባኤ ቃና እንዳስነበብናችሁ ዶ/ር ወርቁ በቤተ ክርስቲያን የሚያሳዩትን ትሕትና በመንግሥት መሥሪያ ቤት እንደሚያሳዩና የዚህ ምሥጢሩ ምን እንደሆነ ጉባኤ ቃና ቃለ መጠይቅ ሲያደርግላቸው "የመኖር ፍልስፍና ከራስ ጋር መስማማት ነው።" ብለው ክርስቲያን ቦታ፣ ጊዜና ሁኔታ የሚወስነው ሳይሆን እሱ ቦታውን፣ ጊዜውንና ሁኔታውን እንደሚወስን በተግባር ያሳዩ መሆኑን ከንባቡ ተረድተናል።

የአስተዳደጋቸውና የክርስቲያናዊ ሰብእናቸው መሠረት ምን እንደሆነ ጉባኤ ቃና ሲጠይቃቸው ካደጉበት ማኅበረሰብ፣ ከቤተ ክርስቲያን እና ባሳለፏቸው የትምህርት ሂደት እንደሆነ መግለጻቸው ይታወሳል።

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሀገራዊ ጉዳይም ኃላፊነታቸውን በትጋት የተወጡ መሆናቸውን ጠቁሞ፣ በሥርዓተ ትምህርት መሥራታቸው ለአገልግሎት ያለውን አበርክቶ ጉባኤ ቃና ሲጠይቃቸው በሙያቸው የማኅበረ ቅዱሳንን የመጀመሪያው የትምህርት ካሪኩለም

መቅረጻቸውን ጠቅሰው ሌሎች በርካታ ትሩፋቶች ለሀገርም ለቤተ ክርስቲያንም እንደሠሩ መግለጻቸውንና በርካታ የሕይወት ተሞክሯቸውን በዝርዝር ማስነበባችንን ልብ ይሏል፡፡

ትዳራቸውን፣ ማኅበራዊ ኀላፊነቶችንና ዘርፈ ብዙ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን በአንድነት አስማምተው ያስኬዱበትን ጥበብ ጉባኤቃና ጥያቄ ጠይቆ፣ በተግባር የተፈተነ የሕይወት ልምዳቸውን ሊያስነብባችሁ በዚህ "እንግዳችን" በሚል ዐምድ አቅርቦላችኊል፤ በማስተዋል እንድታነቡት ይሁን፡፡

**ጉባኤ ቃና፡** እስከ ዶክትሬት የዘለቀ ትምህርት አለ፤ በጎን በኩል አገልግሎት አለ፤ ትዳር አለ፤ ልጆች አሉ፤ ሌሎች ማኅበራዊ ኃላፊነቶች አሉ፤ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥም በመንበረ ጸባዖት የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የሰበካ ጉባኤ አባል ነበርክ፡፡ አሁንም ሰንበት ትምህርት ቤት ታስተምራለህ፡፡ የካ አባዶ ቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ የሰበካ ጉባኤ አባል ነህ፡፡ እና ይህን ሁሉ ነገር እንዴት ማስኬድ ቻልክ? ፈታኝ የሆኑ አጋጣሚዎች አልነበሩም ወይ? እንዴትስ ማለፍ ይቻላል ?

**ዶክተር ወርቁ፡** እርግጥ ነው እሱ፤ በጣም የሚከብዱ የሚመስሉ ነገሮች አሉት፡፡ በሁሉም ዘርፍ መደበኛ መሥሪያ ቤት ብዙ ኃላፊነት አለ፡፡ በማኅበራዊ ሕይወት ከአንተ ብዙ የሚጠብቁ ሰዎች አሉ፡፡ በመንፈሳዊም እዚም እዚያም ለአገልግሎት ትጠራለህ ልክ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ወደ ቤት ስትመጣ እንደ አባወራ ከአንተ የሚጠበቁ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ትልቁ ነገር ጊዜህን በአግባቡ መጠቀም ነው፡፡ በእኔ ግምት ያለሥራ የሚያልፍ ሰዓት መኖር አለበት ብዬ አላምንም፡፡ በሁሉም ጊዜያት የሆኑ የምንሠራቸው ሥራዎች ይኖራሉ፡፡ እነዚያን ሥራዎች ወይ የመሥሪያ ቤት ሥራ ሊሆን ይችላል፤ ወይ ማኅበራዊ አገልግሎት የምንሰጥበት ይሆናል ወይም ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎት

ውስጥ ያለህበት ጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሁሉ ጊዜህን እንደምንም ብለህ በአግባቡ በዕቅድ በመመራት ልማድ ውስጥ ካስገባሃቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለይተህ ቅድሚያ ከተሰጣቸው፤ ኃላፊነትን በአግባቡ የመወጣት ዕድልህ ከፍ ይላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

እኔም በዚያ መሠረት ለመሥራት እጥራለሁ፡፡ በተለይ ደግሞ ወደ ቤተሰባዊ ሕይወት ስትመጣ ቤተሰብ ውስጥ ሳይጎድል ይነስም ይብዛም የምትፈልገውን ዓይነት ሆኖ እንዲቀመጥ አስተዋፅኦ ያደረጉ ሰዎች አሉ፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ባለቤቴ የእኔ እዚህም እዚያም መሯሯጥ ላይ ያላት አስተዋፅኦ እጅግ  ከፍተኛ ነው፡፡ እኔ የምሠራቸው ሥራዎች ተደማምሮ አንዳንዴ ሳስበው እሷ እቤት ውስጥ የምትሸፍነውን ግማሹን የሚሞላ አይመስለኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን በዚህም በዚያም ባሉት ጥረቶቼ ውስጥ የእሷ የኔን ክፍተቶች የምትሸፍንበት እና የምትሞላበት መንገድ እጅግ በጣም ግዙፍ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር በታች የእሷ አስተዋፅኦ እነዚህን ኃላፊነቶች እንድወጣ አስተዋፅኦዋ ለእኔ በጣም ትልቅ ነው፡፡ እና ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ምስጋና የምትወስድ ናት ብዬ አምናለሁ፡፡ ግን እንዳልከው ቀላል አይደለም፡፡ ሁሉም በጣም ጊዜ ይፈልጋል፡፡ ያለንን ሰዓት በአግባቡ ከተጠቀምን ግን ጊዜው በቂ ነው፡፡ በአግባቡ የመጠቀም ጥረት ግን ከእኛ ይጠበቃል፡፡

እኔ ከመደበኛ የሥራ ሰዓቴ ባሻገር ሌሊት አእምሮዬ ደክሞት ማረፍ በሚፈልግበት ሰዓት ካረፍኩ በኋላ ከእንቅልፌ እነሣለሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ልተኛ ብልም እንቅልፍ አይዘኝም፡፡ እውነት ለመናገር የምሠራው ቅድም እንዳልኩት ቅድሚያ ለምሰጣቸው ቅድሚያ በመስጠት፣ መንፈሳዊ ሥራም ከሆነ ቁጭ ብዬ ስጽፍ፣ ሰነድ ወይም የሥልጠና ግብዓቶች (ማቴሪያል) ሳዘጋጅ ላነጋ እችላለሁ፡፡

የመንግሥትም ሥራ ከሆነ እንዲሁ አደርጋለሁ፡፡ ብዙም አይረብሸኝም፡፡ ከእኔ የሚጠበቀውን ሠርቼ ጨርሼ ኃላፊነቴን

እወጣለሁ:: በዚህ ዓይነት መልኩ እዚህም እዚያም ብዙ ሳይጎልብኝ በሰዎች ዘንድ ጥሩ ሠራህ የሚያስብል ሞገስ የሚያሰጥ ነገር አለኝ ብዬ አስባለሁ::

በዚህ ውጤት ላይ የባለቤቱም የልጆቼም እገዛ ቀላል አይደለም፤ በጣም የሚያስመሰግናቸው ነው:: ያ ባይሆን ግን በጣም ይከብዳል፤ እንደ አንድ አካል ተጋግዘን በመሥራታችን የእኔን ሁሉንም ኃላፊነቶች በጥሩ ሁኔታ እንድወጣ አስችሎኛል ብዬ አምናለሁ::

**ጉባኤ ቃና፡** ሥርዓተ ትምህርት የትውልድን ዕጣ ፈንታ የሚወስን መሣሪያ ነው ብለናልና፤ አንተ ደግሞ ማኅበረ ቅዱሳን ባዘጋጃቸው በሦስቱም ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ላይ መሪ በመሆን ተሳትፈሃል:: እና አሁን በተከለሰው ሥርዓተ ትምህርት የግቢ ጉባኤያት ተማሪዎች ምን እንዲሆኑ ትጠብቃለህ?

**ዶክተር ወርቁ፡** እኔ ከሚገርምህ ከመጀመሪያው ሥርዓተ ትምህርት ጀምሮ የምመኘው ሁለተኛውንም ክለሳ ስንሠራ፣ እንዲሁም የአሁኑን ስንሠራ በጣም የምፈልገው እግዚአብሔር ፈቅዶ ብሞት እንኳን አይቆጨኝም የምለው፣ ሆኖም ማየት የምፈልገው ከግቢ ጉባኤ የሚመረቁ ወጣቶቻችን ቤተ ክርስቲያኒቱን በሚገባ ተረድተዋት አሁንም ያለው፣ ነገም የሚመጣው የቤተ ክርስቲያን ችግር ገብቷቸው፣ የቁጭት መንፈስ ያለባቸው ሆነው ቤተክርስቲያን የሚነሡባትን ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡና ከፍ ሲልም ራሳቸው መልስ የሚሆኑ ልጆች ሆነው ባይ ነው::

እና አሁን ያዘጋጀነውን ሥርዓተ ትምህርት ማኅበሩ ካስቀመጠው ስልታዊ ዕቅድ፣ ስትራቴጂክ ፕላን አንጻር ልክ እንዲሆን አድርገን ነው፤ አስበን የሠራነው:: የቀደሙት ሥርዓተ ትምህርቶች የነበሩበትን ጉድለቶች ለመሙላት ጥንካሬዎቹንም ለማጠንከር አስበን ነው የቀረጽነው:: እኛ እንዳሰብነው ከሆነልን እግዚአብሔርም ከባረከልን

ወደዚያ ደረጃ የደረሰ ይሆናል ብዬ ነው የማምነው። ቤተክርስቲያን ብዙ ፈተናዎች ያሉባት ዘመን ላይ ነው ያለነው፤ ለእነዚህ ፈተናዎቿ መልስ የሚሰጡና መልስ የሚሆኑ፣ በአንደበትም በመኖርም መልስ የሚሆኑ ትውልድ ብናፈራ በእነሱ እርሾነት ማኅበረሰቡ እንደ አጠቃላይ ይገነባል ብዬ አምናለሁ። ያንን ማምጣት የሚያስችል እንዲሆን ነው ፍላጎቴ፤ እግዚአብሔር ቢረዳን እንደሱ እናረጋለን ብዬ አስባለሁ።

**ጉባኤ ቃና፦** የቤተክርስቲያንና የሀገር ተረካቢዎች እንዲሁም መሪዎች በማፍራት ረገድ ግቢ ጉባኤያት ሊኖራቸው የሚገባ ሚና ምንድነው?

**ዶክተር ወርቁ፦** እንግዲህ በግቢ ጉባኤያት በሁለት ወገን የተሳሉ ልጆች ይፈራሉ ብዬ አስባለሁ። በአንድ በኩል የአስኳላ ትምህርት ላይ ምንም ሳይሰስቱ በሙሉ አቅማቸው ተምረው ውጤታማ የሆኑ፣ እግዚአብሔር ቢፈቅድ ሁሉም ትልቅ ነጥብ ያላቸው፣ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ ሆነው እንዲወጡ አስባለሁ። በዚያኛው በኩል ያለው ጥረት እና ውጤት ብቃት በተመሳሳይ ሁኔታ በቤተክርስቲያን እንደዚያው ተስለው የቤተክርስቲያኒቷን ትምህርት እና ቤተክርስቲያኒቷን ተረድተዋት ከእነሱ የሚጠበቀውን ለመወጣት ቁርጠኛ የሚሆኑ ልጆች የሚፈሩባት ሆነው ማየት እመኛለሁ። እንዲሆን የምንፈልገውም ያ ነው።

በመደበኛው ሥራቸውም ይሁን በመንፈሳዊ አገልግሎቶቻቸው ቤተክርስቲያን የምትፈልገውን ዓይነት ሰብእና ይዘው በሀገር ልማት እና እድገት ውስጥ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ፣ የትም ቦታ የሚፈለጉ ዓይነት የግቢ ጉባኤ ምሩቃን ሆነው ማየት እመኛለሁ።

ሥነ ምግባር ያላቸው፣ ከክፉ ነገር ራሳቸውን የሚጠብቁ፣ ለሀገር ለወገን የሚያስቡ፣ ሀገር ወገንን የተፈጠሩለት ለዚያ እንደሆነ የሚያምኑ፣ ሰው ለራሱ ብቻ እንዲኖር አይደለም እግዚአብሔር

የፈጠረው:: እውነት ለመናገር ለሌላም ሰው እንዲኖር ነው:: የፍቅር ትርጉሙም ያ ነው:: የፍቅር ትርጉሙም ክርስቶስ ነው:: ከፅንሰቱ እስከ ዕርገቱ ያስተማረን ለሌሎች መኖርን ነው እንጂ “ሆዴ ይሙላ፣ ደረቴ ይቅላ፤ እኔ ብቻ ይድላኝ” የሚል አይደለም:: እንዲፈጠር የሚታሰበው የግቢ ጉባኤ ተማሪ እሱ ነው::

ግን አሁን ጭልጥ ያለ ካፒታሊስት አስተሳሰብ ውስጥ ተገባና እኔ ብቻ ይድላኝ የሚል የእነዳርዊን “survival of the fittest ፤ ለሁኔታዎች ብቁ የሆነው(አሸናፊው) ይኖራል” የሚለው ትምህርት ዓለም የምትመራበት ሥርዓት ሆኖ ተበላሸን እንጂ ሰዎች ስንፈጠር በእግዚአብሔር አምሳል እግዚአብሔርን በመምሰል ውስጥ ነው::

ራሱ ክርስቶስ ለሰው ልጆች መኖርን እንዴት እንደሆነ በአንደበቱ በምድር ላይ በዘመነ ሥጋዌ በምድር ሲመላለስ በተግባር አሳይቶን ነው የሄደው፤ ይህንን ነው ልንከተል የሚገባው፤ አባቶቻችን እናቶቻችን የቀደሙት በዚህ ልክ ነው ኖረው ያሳዩን:: “ሃይማኖትህን ካድ” ሲሉት ሃይማኖቴን ከምክድ ‘ሥጋዬን ከነፍሴ ለዩ’ እስከማለት ደርሰው በሰማዕትነት ያለፉት እናቶቻችን አባቶቻችን ሁሉ ነገራቸው ሕገ እግዚአብሔርን፣ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በመጠበቅ ኖረው ነው ያለፉት:: የግቢ ጉባኤ ምሩቃን ይህንን አሠረ ፍኖት የሚከተሉ መሆን አለባቸው ብዬ ነው የማስበው::

የግቢ-ጉባኤያት ሚናቸው ወደዚህ ከፍ ማለት አለበት:: ተጽዕኖ ፈጣሪ ትውልድ መፈጠር አለበት ብዬ አምናለሁ:: በዚያ ልክ ሲሆን ዓላማችን ተሳካ የሚል እምነት አለኝ::

**ጉባኤ ቃና፦** የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍ ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር የሚጋጭ የሚመስላቸው ብዙ ሰዎች አሉ:: እና “ሃይማኖተኛ እንዴት ፖለቲከኛ ይሆናል?” ለሚሉ አስተሳሰቦች ሐሳብህ ምን ይመስላል? በእውነት ሰው ከፖለቲካ ራሱን ገለልተኛ ማድረግ እና መራቅ ይችላልን?

ዶክተር ወርቁ፡ ትልቁ ነገር የግድ የሆነ ፓርቲ አባል መሆን ይገባል ብዬ አላምንም:: እኔ አንዳንድ ጊዜ ስለ ፖለቲከኞች ሲታሰብ የፓለቲካ ፓርቲ አባል ካልተኮነ ፖለቲካ ውስጥ ሚና ያለው ሰው የማይመስለው እንዳለ አስተውላለሁ:: በእኔ እምነት የግድ የፓርቲ አባል መሆን አይጠበቅብህም:: ግን ባለህበት እግዚአብሔር ባስቀመጠህ የኃላፊነት ቦታ ላይ ስትቀመጥ ቤተ ክርስቲያንንም በተለይ ደግሞ ሕዝብን ማገልገል ምን ማለት እንደሆነ ገብቶን በዚያ ልክ ሕዝብን ማገልገል ከቻልን እና በዚያ አገልግሎት ውስጥ ደግሞ ተጽዕኖ መፍጠር ከቻልን የምንሰማ፣ የምንደመጥ ከሆንን ፖለቲካ እና ፖለቲከኞች የሚያመጡትን የተሳሳተ አስተሳሰብም ሆነ ትምህርት ማስቆም የምንችል ይመስለኛል:: በተለይ ቁጥራችን በጨመረና በበዛን ቁጥር እውነት እኮ ነው፤ እነሱ የሚናገሩት ትክክል እኮ ነው የሚል ማኅበረሰብ እየፈጠርክ ትሄዳለህ::

አሁን ችግር የሆነው እንደ ሀገርም እንደ ዓለምም ብንመለከተው የስሕተት ትምህርቶች በመጽሐፍ ተጽፈው በትምህርት ቤትም ቁም ነገር ሆነው ሲነገሩን እውነት እየመሰሉን ሄደዋል:: እነዚህ ነገሮች እውነት አለመሆናቸው የጥፋት እና የክፋት መንገድ መሆናቸው ለማሳየት አንድ ሁለት ሦስት እየተባለ ቁጥሩ የበዛ በዚህ አስተሳሰብ የተቃኘ ማኅበረሰብ መፈጠር አለበት ብዬ አስባለሁ::

ዓለም አሁን ከምትመራበት የsocial realism theory ስሕተት መሆኑንም እያሳየህ ትሄዳለህ:: ምክንያቱም ጥፋትንና ውድቀትን እንጂ ከዚህ ምንም አታገኝም:: ጉልበት ያለው ይኖራል፤ ጉልበት የሌለው አይኖርም:: ለምን እንዲህ ዓይነት ጉልበተኛ የበዛበት ዓለም ይፈጠራል? ከእሱ ይልቅ ያንተ ጉልበት ለእኔ የእኔ ጉልበት ላንተ፣ የእኔ ዕውቀት ላንተ፣ ያንተ ዕውቀት ለእኔ ሁለቱን አደጋግፈን አስተባብረን በኅብረት ሁላችንም ስኬታማ የምንሆንበትን ዓለም ለምንድን ነው የማንፈጥረው? በሚል ለዓለም ኅብረተሰብ እያስተማርን

የፖለቲካውን ስሕተት በማሳየት ከውድድር እና ከአሸናፊነት መንፈስና በግለሰብ ከሚመጣው የበላይነት ይልቅ የጋራ አሸናፊነትና የጋራ ስኬት ወደሚያበሥር አስተሳሰብ እንዲመጡ የሚያስችል ተጽዕኖ በፖለቲካውም በፖለቲከኛውም ውስጥ መፍጠር ከተቻለ ሌላ ቀርቶ ሕገ መንግሥቱ የማሻሻል ረገድ ውስጥ ትገባለህ።

አሁን የምናየው የተሻለ ዕድል ያላቸው ሰዎች፣ በተሻለ ትምህርት ቤት ተምረው በተሻለ የሥራ መስክ ውስጥ ገብተው የተሻለ ተከፋይ ሆነው፣ እያንዳንዱ ያመጡትን ስኬት ተብዬ ነገር በገንዘብ ብዛት እና በሀብት በሚሉት ነገር አትለካውም። ስኬት ያለው እግዚአብሔርን በማስደሰት ውስጥ ነው ብዬ አስባለሁ። እግዚአብሔር ማስደሰት ማለት ደግሞ ፊት ለፊትህ ያለውን ወንድምህን እኅትህን ማስደሰት ነው። የተራብ አንተ በምታደርገው ነገር ጠግቦ "ውይ አንተ እኮ ለእኔ እንዲህ አበርክተህልኛል እግዚአብሔር ይስጥህ" ሲባል መስማት እኮ ትልቅ ነገር ነው። ከዚያ አልፎ ደግሞ ውድቀት ላይ ያለ ሰው ከውድቀቱ ወጥቶ ወደተሳካ ሕይወት በመግባት ከራሱ አልፎ ለሌላው ማምጣት ሲችል ያ ትልቅ ስኬት ነው። ከውድቀት አነሣኸኝ፤ ከአመድ ተነሣሁ፤ በአንተ ድጋፍ የሚልን ማኅበረሰብ ማየት እኮ ትልቅ ነገር ነው። አሁን ኢትዮጵያ እንደዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ ትፈልጋለች። ፖለቲካውንም በዚህ ዓይነት መልኩ መቀየር ማሻሻል የሚቻልበትን ሥራ መሥራት ይቻላል ብዬ አስባለሁ።

እና እነዚህን ስትሠራ የፖለቲካ አስተሳሰብ ራሱ ቅኝቱ ከዚያ ወጥቶ መንፈሳዊ የሚመስል የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ የማንገባበት ምንም ምክንያት አይኖርም። አሁን ትልቁ ነገር ምንድ ነው? እንዲህ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች ከአስተዳደር ሥርዓቱ ራሳቸውን እያገለሉ በወጡ ቁጥር ሌላው በልቼ ልሂድ የሚለው የዳርዊንን ሐሳብ የሚተገብር በበዛ ቁጥር አሁን እንደሚታየው ነው። ልክ ዳርዊን እንደሚለው "ሰው በዝግመተ ለውጥ ዝንጀሮ ከሚመስል እንስሳነት

ወደ ሰውነት መጣ ይላሉ። የሰው ልጅ ወደዝንጀሮ የሚጠጋ ዝንጀሮ የሚመስል ጠባይ ያለው ነው፤" ዝንጀሮ ደግሞ ያሸነፈ የሚኖርበት ማኅበር ዓይነት አኗኗር የሚኖር እንስሳ ነው።

ዝም ብለህ የዝንጀሮ መንጋን ብትመለከት ዘግናኝ ነው፤ በተለይ አንድ ወንድ የዚያ ቡድን መሪ ይሆንና ሌሎቹ ሴቶች ናቸው የሚሆኑት፤ ወንዶችን ቀጥቅጦ ገዝቶ ነው ያንን የበላይነት የሚያስከብረው።

የሰው ልጅ እንዴት ከዝንጀሮ ይማራል? ቀጥቅጦ መግዛትን ከዝንጀሮ የተማረ እስኪመስል ድረስ የዝንጀሮ ጠባይ እንዲይዝ የተደረግንበት አንዱ ማሳያ የፖለቲካው ወደዚያ ዓይነት ጽንፍ መሄዱ ነው። ከዚያ ዓይነት አካሄድ እንድንወጣ በዚህም በዚያም በአንድም በሌላ መንገድ እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ ስሕተት መሆኑን ማሳየት የሚችል ማኅበረሰብ መገንባት አለብን ብዬ አስባለሁ።

ያኔ ወደ ቀናው የፖለቲካ አስተሳሰብ ውስጥ በመግባት ሁሉ ተባብሮ፣ በጋራ ሠርቶ በጋራ የሚሳካለት ማኅበረሰብአዊ እይታ ይመጣል። አንዱ የሌላውን፣ የሀገርን ወይም ሀገር ከምንለው ጀርባ ያለውን የሕዝብ ሀብት ዘርፎ እኩለ ሌሊቱ ሙሉ ሲጠጣ አድሮ፣ ዝሙት ሠርቶ፣ እንደድሎት ቆጥሮ ከሚኖር ይልቅ፣ "ይህ ገንዘብ የሕዝብ ንብረት ነው የሀገሬ ነው" ወደሚል አስተሳሰብ መጥቶ መሬት የወደቀውን ወንድም እኅቱን፣ እናት አባቱን ከመሬት በማንሣት፣ እንዲያውም ወደ እርሱ ደረጃ ከፍ በማድረግ ከብረን በጋራ የምንኖርበት አስተሳሰብና አሠራር ከቻልን ፖለቲካውን አስተካከልን ብዬ አስባለሁ።

እንደዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ማኅበረሰብ "ሆዴ ይሙላ ደረቴ ይቅላ" ከሚል የዝንጀሮ አስተሳሰብ ወጥቶ የሰውነትን ክብር ወደ ሚሰጥ ማንነት መምጣት አለበት። ሰውነት ገና ከትንሽ ነገር ይጀምራል። በዕድሜ ትንሽ ሆነ ትልቅም ሆነ፣ አረጀ ወጣትም ሆነ፣ ገንዘብ ኖረውም አልኖረውም፣ ሰው መሆን በራሱ ክቡር ነው።

በዚህ ዓይነት መልኩ ካገኘው አካፍሎ አብረን እንብላ የሚለው ማኅበረሰብ መፍጠር እንዲቻል በዚህ የተቃኘ ማኅበረሰብአዊ መፍጠርና ማብዛት አለብን ብዬ አስባሁ። ያን ጊዜ ፖለቲካው ላይ ተጽዕኖ ፈጥረን። ሀገር ትመራለች የሚባለው ሕገ መንግሥት በዚህ ዓይነት መልኩ የተቃኘ ማድረግ የሕዝብ ገንዘብ የሚዘርፈውንም ደግሞ ከስብእና በታች እንደወረደ ሁሉ ቆጥሮ የሚገባውንም ቅጣት የሚቀጣበት የሕግ ሥርዓት የማምጣት የምታስችልበት ዕድል አለ። እንደዚያ ማድረግ ስትችል እየበዛህ እየበዛህ ስትሄድ በጣም እየተጸየፍክና እያስተካከልከው ትሄዳለህ።

ያንን የክፋት መንገድና አስተሳሰብ የሚጸየፍ ማኅበረሰብ ይኖራል ብዬ አስባለሁና የተማረው ትውልድ መጀመሪያ ራሱን መፈተሽ አለበት። ሰውነት በእግዚአብሔር አምሳል መኖር ነው፤ እግዚብሔርን መምሰል ነው፤ እግዚአብሔርን መስሎ ለመኖር መትጋት ነው፤ እግዚአብሔር ከሚፈልገው ሙሉ ለሙሉ ራሱን አስወጥቶ ራሱን በሆዳምነት መስመር ውስጥ የከተተ ሰው ነኝ ብሎ ማሰብ አለበት ብዬ ላስብም። ስለዚህ ከዚያ ቅኝት እንዲወጣ የሚያደርግ ማኅበረሰብ እያበዛን በሄድን ቁጥር በእኔ ግምት ፖለቲካውንም እንቀይራለን ብዬ አስባለሁ።

አሁን ትልቁ ነገር ያኛው ጎን በዛ፤ እንዲህ ብሎ የሚያስብ ማኅበረሰብ ቀንሷል፤ ስለዚህ በቀነሰ ቁጥር ያኛው ሐሳብ በፖለቲካ ውስጥ እውነት መስሎ ገባ። እና እሱ አስተሳሰብ፣ የውድቀቱ አስተሳሰብ እንደ እውነት ተቆጥሮ በዚያ መልኩ በመሄዳችን አሁን የምናየው ድህነት፣ ችግር ወዘተ. የዚያ ውጤት ነው የሚል ምልከታ አለኝ። እንጂ ሀገራችን ብዙ ተፈጥሯዊ ጸጋ ያላት ናት። ያንን ተፈጥሯዊ ጸጋ በአግባቡ መጠቀም እንድንችል እንደ አንድ ልብ መካሪ፣ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ የሚሆን ማኅበረሰብ መፍጠር ብንችል ብዙዎቹ ችግሮቿ ይፈቱ ነበር የሚል እምነት አለኝ።

እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ማኅበረሰብም እየጨመረ እየጨመረ ይሄዳል። ቅድም እንዳልኩት በሁለት ወገን በሃይማኖቱም በአስኳላውም የተሳሉ፣ ተሰሚነት ያላቸው ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ወጣቶችንም እያበዛን መሄድ አለብን እንጂ ሦስት ሺህ ዓመትና ከዚያ በላይ ዓመታት አብረን እንዳልኖርን ይህ የእኔ አይደለም የሚል ዓይነት አስተሳሰብ ውስጥ በጋራ በመኖር ውስጥ ስኬት ማምጣት የሚያስችለውን መንገድ የተወ ትውልድ እያበዛን ስለመጣን ነው። ያን ትውልድ መቀነስ አለብን። የምንቀንሰው አስተሳሰቡን እያሻሻልንለት ነው።

ነገር ግን ከዚህ የመጠፋፋት መንገድ ወጥተን ለካስ በጋራ ሠርቶ ፣ በጋራ ስኬት ውስጥ መግባት ይቻላል የሚል አስተሳሰብንም ከዚያ አስተሳሰብ በኋላ ደግሞ ተግባራዊ ምላሽንም መፍጠር ከቻልን ኢኮኖሚው ፖለቲካውን፣ ፖለቲካው ኢኮኖሚውን ራስ በራሳቸው እየተደጋገፉ በተሳካ መንገድ መሄድ እንችላለን ብዬ አምናለሁ።

በዚህ ዓይነት መልኩ የፖለቲካውንም ተጽዕኖ ማሸነፍ ያለበት ዕድል እንዳለም አምናለሁ። አሁን ይህንን ሲያዩት በጣም ሩቅ ነው ግን ቢተገብሩት እጅግ ምቹና ለችግሩ ዓይነተኛ መፍትሔ ነው።

ጉባኤ ቃና፡ ዶክተር በመጨረሻም ለወጣቱ እንዲሁም ያንተን የትምህርት ሙያ ዘርፍ መከተል ለሚፈልጉ ተማሪዎች የምታስተላልፈው መልእክት ካለ

ዶክተር ወርቁ፡ ወጣቶች የመኖር ፍልስፍናቸውን ነው ማስተካከል ያልባቸው። ይህ ማለት ደግሞ ከራስ ጋር መስማማት ነው ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም የመኖር ፍልስፍና በብዙ መልኩ ብዙ ጉዳይን ይወስነዋል። የመኖር ፍልስፍና ጠባይንም፣ ሥራንም፣ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ይወስናል የሚል እምነት አለኝ።

ሰው ሰውን መውደድ፣ ማፍቀርና ማክበር አለበት። እግዚአብሔርን መምሰል ከዚህ ጋር ይያያዛል። ወጣቶችም ይህን ነገር ተገንዝበው የመኖር ፍልስፍናቸውን ከዚህ ሐሳብ ጋር ማስተካከል ይኖርባቸዋል።

ከቤተ ክርስቲያን አባቶች የተማርነው ጠንክሮ መማርን፣ መሥራትን፣ ሰውን ያለዋጋ መውደድን፣ ስለሆነ ወጣቶችም ይህን ፈለግ በመከተል ለእግዚአብሔርም ለሰውም የተመቸ አካሄድን መከተል አለባቸው ።

በተሰማሩበት የሙያ መስክ በሙሉ እግዚአብሔርን በመፍራት በትጋት ያለ ስስት ማገልገል ይኖርባቸዋል። በመደበኛው ሥራቸውም ይሁን በመንፈሳዊ አገልግሎቶቻቸው ቤተክርስቲያን የምትፈልገውን ዓይነት ሰብእና ይዘው በሀገር ልማት እና እድገት ውስጥ ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ፣ የትም ቦታ የሚፈለጉ ዓይነት የግቢ ጉባኤ ምሩቃን ሆነው ማየት እመኛለሁ።

ሥነ ምግባር ያላቸው ከክፉ ነገር ራሳቸውን የሚጠብቁ ለሀገር ለወገን የሚጨነቁ የሚያስቡ ሀገር ወገንን የተፈጠሩለት ለዚያ እንደሆነ የሚያምኑና በዚያ ልክ ተግተውና ጠንክረው በመሥራት ራሳቸውን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ሀገርን ሊያገለግሉ ይገባል።

**ጉባኤ ቃና፦** ዶክተር እግዚአብሔር ይስጥልን፤ እግዚአብሔር ያክብርልን፤ ውድ ጊዜዎን ሠውተው ይህንን ቃለ መጠይቅ ስላረጉልን በጣም እናመሰግናለን።

**ዶክተር ወርቁ፦** እሺ፤ እኔም ከልብ አመሰግናለሁ።

# ብሂለ አበው

- ቤተ ክርስቲያን መጠጊያችን ነች፤ ቤተ ክርስትያን የኖኅ መርክብ ነች፤ በውስጧ እንጠለላለን፤ ከውጭዋ ግን ማዕበልና ቀላያት ተከፍተዋል። (ቅዱስ እንድርያስ)
- አስተዋዮች ዐዋቂዎች ጥበበኞች ጸሓፍት ሀገር አይመዝበር፤ ሕዝብ አይበደል፤ ሕዝብ አይናቅ፤ ሕዝብ ከሕዝብ አይበላለጥ፤ ሕዝብ አይፈናቀል፤ ነፃነት ይኑር፤ ሰላም ይስፈን . . . ስላሉ በመንግሥት ሲወነጀሉ፣ አሸባሪ ሲባሉ ተወንጅለውም ሲገረፉ በእስር ሲማቅቁ ከሀገር ተገፍተው ሲወጡ - ያኔ ጥበብም ተሰደደች ማለት ነው። (አንጋረ ፈላስፋ)
- ያልገደለ እጅ ግን ያላዳነ፣ ያልሰረቀ እጅ ግን ያልመፀወተ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ የለውም። እውነተኛው መልካምነት ክፉ አለማድረግ ብቻ ሳይሆን መልካም ማድረግም ነው። የሚጎዳንን መተው ብቻ ሳይሆን ስለ ሌሎች ጥቅም መድከምም ነው። (አባ ሺኖዳ ሣልሳዊ)
- ቂመኛ የሚጸልየው ጸሎና ገበሬ በባሕር ዘርቶ አጭዶ የሚያገኘው ምርት እኩል ነው። (ማር ይስሐቅ)
- መመጽወትና መጾም ለነፍስ ሕይወትን ለሥጋ ጤንነትን ይሰጣል። (አንጋረ ፈላስፋ)

# የጥያቄዎቻችሁ መልስ

በዲ/ን አብርሃም ባንቲሁን

**ጥያቄ፡-** "እኛ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ክፍተቶችን ስናገኝ በተለይ ለሁለት ወራት ወደ ቤተሰብ ለዕረፍት ስንመለስ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እንፈልጋለን፤ ግን ምንም እንኳ ፍላጎቱ ቢኖረንም ከየት መጀመር እንዳለብን እንኳ አናውቅም፤ እንደውም አንዳንድ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ አታንብቡ ትሰናከላላችሁ" ይሉናል፤ በጉባኤ ቃና መጽሔታችሁ ምላሽ ቢሰጠን።

**መልስ፡-** ይህ እጅግ በጣም ወቅታዊ እና በግቢ ጉባኤ ሕይወት ውስጥ ብዙ ተማሪዎችን የሚፈታተን ትልቅ ጥያቄ ነው። በዕረፍት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብና ለመረዳት መሻታችሁ የሚበረታታ ድንቅ ፍላጎት ነው።

በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት፣ ከቅዱሳት መጻሕፍት እይታ አንጻር የተውሰኑ ነጥቦችን እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታለን።

## 1. "መጽሐፍ ቅዱስ አታንብቡ፣ ትሰናከላላችሁ"

አንዳንድ ሰዎች ከበጎ ቅንዓት ወይም ካለመረዳት የተነሣ "መጽሐፍ ቅዱስን አታንብቡ፣ ትስታላችሁ" ይላሉ። ነገር ግን ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይነበብ አታግድም፤ ይልቁንም እንዴት መነበብ እንዳለበት ትመራለች እንጂ።

ውድ የግቢ ጉባኤ ልጆች፦ ቅዱሳት መጻሕፍትን አለማንበብ ራሱ ለስሕተትና ለጥፋት እንደሚዳርግ ጌታችን በግልጽ የተናገረዉን እንመልከት፦

“መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ” (ማቴ. ፳፪ ፥፳፱)

ቅዱስ ጳውሎስም ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅም እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፦

“አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን ዐውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።” (፪ኛ ጢሞ. ፫፥፲፭-፲፯)

ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በተመሳሳይ ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያነቡ ሰበብ ሲፈልጉና ሲፈሩ በጥብቅ ይገሥጻቸው ነበር። በእርሱ ዘመን የነበሩ ሰዎች “እኛ ዓለማውያን ነን፣ ሚስትና ልጆች አሉን፣ መነኮሳት አይደለንም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ የእነርሱ ሥራ ነው” ሲሉ እርሱ ግን እንዲህ ብሏል።

“ይህ መጻሕፍትን አለማንበብ ሰይጣን የፈጠረው ሰበብ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይበልጥ የሚያስፈልገው በዓለም ውስጥ ለሚኖሩት፣ በውጊያና በፈተና መሐል ላሉት ለእነርሱ ነው… መጽሐፍ ቅዱስን አለማወቅ ታላቅ ገደልና ጥልቅ ጥፋት ነው።” (Homilies on Matthew)

ስለዚህ፦ መሰናክል የሚመጣው መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ሳይሆን፣ በገዛ ዕውቀትና በትዕቢት ተመርኩዞ የራስን ትርጉም ለመስጠት ሲሞከር ነው።

## 2. መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ልንከተላቸው የሚገቡ ሕጎች (ቅድመ ሁኔታዎች) ምንድን ናቸው?

### በትሕትና እና በጸሎት መጀመር

ንባቡን ከመጀመራችን በፊት "አቤቱ ልቡናዬን አብራ" ብሎ መጸለይ ያስፈልጋል። ቅዱስ ዳዊት "ለባሪያህ መልካም አድርግ፤ ሕያው እንድሆን፥ ቃልህንም እንድጠብቅ ዓይኖቼን ክፈት፤ ከሕግህም ተአምራትህን አያለሁ፤ እኔ በምድር እንግዳ ነኝ፤ ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።" (መዝ. ፻፲፰፥፲፯-፲፰)

### ከቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ አለመውጣት

መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ነው፤ በመሆኑም በግል ስሜትና ዕውቀት ፈጽሞ መተርጎም አይቻልም። ቅዱስ ጴጥሮስ በግልጽ እንዳስተማረው፦ "በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም" (፪ኛ ጴጥ. ፩፥፳) ይህ ኃይለ ቃል ለዚህ ማረጋገጫ ነው ።

### የማናውቀውን ጠይቆ መረዳት

በሐዋርያት ሥራ ላይ ተጽፎ እንደምናገኘው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበረ። ቅዱስ ፊልጶስ "በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" ባለው ጊዜ፣ ጃንደረባው የመለሰው መልስ ለኦርቶዶክሳውያን ትልቅ መመሪያ ነው፤ "የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል?" (ሐዋ. ፰፥፴-፴፩) እንዳለ እኛም የማንረዳውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለአባቶችና ለመምህራን በማስታወሻ ይዘን መጠየቅ ይገባል።

### ፫. የሁለት ወራት የዕረፍት ጊዜ አነባብ ዕቅድ (Practical Guide)

"ከየት እንጀምር?" ለሚለው ጥያቄአችሁ፣ ለሁለት ወራት (፷ ቀናት) የሚሆን ስልታዊና ቀላል የአነባበብ ፍሰት በከፊሉ እንመልከት።

#### ሀ. የመጀመሪያው ወር (ወደ አዲስ ኪዳን መግቢያ)

በቀጥታ ከብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ለምሳሌ ከትንቢተ ሕዝቅኤል መጀመር ግራ ሊያጋባ ይችላል። ስለዚህ ከአዲስ ኪዳን ታሪኮች መጀመር ይመረጣል፤ ከሐዲስ ኪዳንም ያለ አበው ትርጓሜ ራእይን ቢያነቡ ለመረዳት ያስቸግራል።

አንደኛ እና ሁለተኛ ሳምንት፦ ከ፬ቱ ወንጌላት አንዱ የሆነው የማቴዎስ ወንጌል ማንበብ (አብዛኞቹ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶችን ከዚህ መጽሐፍ ያገኛሉ።)

ሦስተኛ ሳምንት፦ የሐዋርያት ሥራ (የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና የሐዋርያት ጉዞ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ያስችላል።)

አራተኛ ሳምንት፦ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክቶች (በተለይ ሮሜ፣ ቆሮንቶስ፣ ገላትያ) እና የቅዱስ ያዕቆብ መልእክት (ለዕለት ዕለት ክርስቲያናዊ ሕይወት ተግባራዊ ምክር የሚሰጥ እንደ ወጣኒነታችን ለተግባራዊ ክርስትና ያግዘናል።)

#### ለ. ሁለተኛው ወር (ታሪክና የጥበብ መጻሕፍት)

አምስተኛና ስድስተኛ ሳምንት፦ ኦሪት ዘፍጥረት (የዓለም መፈጠር፣ የአባቶች ታሪክ) እና ኦሪት ዘጸአት (የእስራኤል ከግብፅ መውጣት(ይህ ለክርስትና ሕይወት ጉዞ ምሳሌ ነው።)

ሰባተኛና ስምንተኛ ሳምንት፦ የምሳሌ መጽሐፍ (ለወጣቶች እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የጥበብ ምክሮች ያሉበት) እና የየዕለቱ መዝሙረ ዳዊትን አብሮ መጸለይ።

አነስተኛ ግብ ማስቀመጥ፦ መጽሐፉን ለመጨረስ መሮጥ ሳይሆን ከመረዳት ጋር ያንብቡ፤ ብዙ ከማንበብ ይልቅ በጥንቃቄና በማስተዋል ማንበብ ይመረጣል፤ ለዕውቀት ብቻ ሳይሆን ተረድቶ ለመለወጥ ማንበብ ያስፈልጋል።

በአባቶች መጻሕፍት መታገዝ ፦ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ የሃይማኖት መጻሕፍትን (ለምሳሌ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ የቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ኤፍሬም የሌሎችም አባቶች መጻሕፍት) ጎን ለጎን ማንበብ መንገዱን የተቃና ያድርገዋል።

ውድ የግቢ ጉባኤ ልጆች፦ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውና ተነቦ አይጠገብም፤ ተተርጉሞም አያልቅም። እስከ ዛሬ የተነሡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ተርጕመው ከነገሩን ነገር በተጨማሪም አዲስ ነገር እስከ ዓለም ፍጻሜ የሚነሡ ሌሎች ሊቃውንት ይነግሩናል። የማይለዋወጥ እና አዲስ የማይሆነው ነገር ቢኖር መሠረታዊ እምነታቸው እና ሐሳባቸው ነው። እስከ ዓለም ፍጻሜ ማንም ቢነሣ ከቀደሙት አበው ትምህርት እና መሠረተ እምነት ጋር የሚጋጭ ሆነ የሚቃረን ነገርን ካመጣ ያ ሐሳብ እነርሱን ካነሣሣቸው መንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ እንረዳለን። መንፈስ ቅዱስ እርስ በርሱ አይጋጭምና።

መጽሐፍ ቅዱስን በተሻለ መልኩ ለመረዳት ሰባት ነገሮች መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

**፩ኛ. የመጽሐፍ ቅዱስ መልክዓ ምድር** (Biblical Geography)

መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰነ ምድር፣ ተራራ፣ ወንዝ እና ከተማ ውስጥ የተፈጸሙ ታሪኮችን የያዘ መጽሐፍ ነው።

ጥቅሙ፡- የአንድን ታሪክ መልከአ ምድራዊ አቀማመጥ ማወቅ የምሥጢሩን ጥልቀት ለመረዳት ይረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- ጌታችን በምሳሌው "አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ" ሲል ኢየሩሳሌም ከተራራማ ቦታ ላይ የምትገኝ፣ ኢያሪኮ ደግሞ ወደ ታች ዝቅ ብላ በደልዳላ ቦታ የምትገኝ መሆኗን ማወቅ፣ ታሪኩን በዓይነ ሕሊናችን እንድንሥለውና "ከፍታ ካላት ከቅድስት ከተማ (ከገነት) ወደ ዝቅታና ወደ ምድር የወረደውን የአዳምን ታሪክ" በምሥጢር እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ (ሉቃ. ፲፥፴) ወንጌላትን ስናነብ የቅዱሳን ቦታዎችን (እንደ ገሊላ ባሕር፣ ዮርዳኖስ ወንዝ፣ ደብረ ዘይት ተራራ) አቀማመጥ በካርታ ለማየት መሞከር መልካም ነው፡፡

## ፪. የመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቦች ታሪክ (Biblical History)

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በተለያዩ ዘመናትና በነገሥታት ታሪክ ውስጥ አልፈው ነው፡፡ የአይሁድ፣ የግብፅ፣ የአሦር፣ የባቢሎን፣ የፋርስና የሮማውያን ታሪክ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡

ጥቅሙ፡- በሐዲስ ኪዳን ወንጌል ውስጥ የአይሁድ ማኅበረሰብ በሮማውያን የቅኝ አገዛዝ ሥር እንደነበረ መረዳት፣ ሕዝቡ ምን ዓይነት መሲሕ ይጠብቅ እንደነበረ (የፖለቲካ ነጻ አውጪ) እና ጌታችን የመጣበትን ሰማያዊ ዓላማ ለምን ሊረዱት እንዳልቻሉ በግልጽ እንድንረዳው ያግዘናል፡፡ ለምሳሌ፡- "ኢየሱስም በይሁዳ ቤተ ልሔም በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን በተወለደ ጊዜ፥ እነሆ፥ ሰብአ ሰገል፡፡ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና እያሉ ከምሥራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፡፡"(ማቴ. ፪፥፪)

ስለዚህ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች ለዕረፍት ሲወጡ፦ በወንጌል ውስጥ “ሄሮድስ”፣ “ጲላጦስ” ወይም “ቀያፋ” የሚሉትን ስሞች ሲያገኙ፣ በዚያ ዘመን የነበራቸውን ታሪካዊ ሚና አስተውለው ቢመጡ በኮርስ መርሐ ግብር እንዲሁም ከመምህራን በመጠየቅ የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብና ትርጉም በቀላሉ ለመረዳት አይቸገሩም።

### ፫. የመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቦች ባህል (Biblical Culture)

እግዚአብሔር ለሰዎች የተናገረውና የተገለጠው በሰዎች ቋንቋና ባህል ውስጥ ሆኖ ነው። የጥንቱ መካከለኛው ምሥራቅ ባህል፣ የጋብቻ ሥርዓት፣ የግብርና ሕይወት፣ የአመጋገብና የሰላምታ ልውውጥ ዛሬ ካለንበት ባህል የተለየ ነው።

ጥቅሙ፡- ለምሳሌ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ላይ የወይን ጠጅ ማለቅ ለአስተናጋጆቹ ምን ያህል ትልቅ የባህል ውርደት እንደነበረ መረዳት፣ ድንግል ማርያም ያሳየችውን የራኅራኄና የምልጃ ሚና ይበልጥ እንድናደንቅ ያደርገናል። (ዮሐ. ፪፥፫)

### ፬. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ እንስሳት ጥናት (Biblical Zoology)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ እንስሳት ለምሳሌ፡- ለምስጋና፣ ለትምህርት ወይም ለምሳሌነት ተጠቅሰዋል።

ጥቅሙ፡- ጌታችን “እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ” ሲል የእባብንና የርግብን ተፈጥሮ ማወቅ ክርስቲያናዊ ጥበብን እንድንረዳ ያደርገናል። ርግብ የዋህ ናት፤ ቂም አትይዝም፤ እባብ ልባም ነው፤ ጭንቅላቱን ይጠብቃል፣ ቆዳውን (አሮጌ ማንነቱን) ይገፈፋል። (ማቴ. ፲፥፲፮)

ውድ የግቢ ጉባኤ ተማሪዎች! በዕረፍታችሁ ወቅት ወንጌልን ስታነቡ፡- ወንጌል ላይ የሚጠቀሱትን በግ፣ ፍየል፣ ቀበሮ ፣ ንስር የመሳሰሉት እንስሳት ተፈጥሮ እያስተዋላችሁ አንብቡ።(ለምሳሌ፡- ሄሮድስን ቀበሮ ያለው ለምንድነው? የሚለውን ጭምር መመርመር። (ሉቃ. ፲፫፥፴፪)

## ፲. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ዕፀዋት ጥናት (Biblical Botany)

ዕፀዋት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትልቅ ቦታ አላቸው። ከዕፀ ሕይወት ጀምሮ እስከ ጌታችን የመስቀል ዕንጨት፣ የሾላ ዛፍ፣ የበለስ ዛፍና የወይን ተክል በወንጌል ውስጥ በስፋት ይገኛሉ።

ጥቅሙ፡- ጌታችን "እኔ እውነተኛ የወይን ተክል ነኝ" ሲል፣ የወይን ተክል ቅርንጫፍ ከግንዱ ካልተጣበቀ በስተቀር ፈጽሞ ሊያፈራ እንደማይችልና ደርቆ እንደሚቃጠል ማወቅ፣ እኛም ከቤተ ክርስቲያንና ከክርስቶስ (በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን) ከተለየን ሕይወት እንደሌለን የሚያሳይ ታላቅ ትምህርት ነው። የበለስ ዛፍ ቅጠል ብቻ አውጥታ አለማፍራቷና መረገሟም የግብዝነት ምሳሌ መሆኑን እንረዳለን። (ዮሐ. ፲፭፥፩-፬)

፲፩. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ማዕድናት ጥናት (Biblical Mineralogy)

ወርቅ ጨው፣ ዕንቍ እና የተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምሳሌነትና በታሪክነት ይጠቀሳሉ።

ጥቅሙ፡- ሰብአ ሰገል ለሕፃኑ ጌታ ያቀረቡት "ወርቅ፣ ዕጣንና ከርቤ "ምንነታቸውንና ተፈጥሯዊ ጥቅማቸውን ስናጠና ምሥጢሩ ግልጽ ይሆንልናል። ወርቅ ለንግሥናው (ንጉሥ ነውና) ፣ ዕጣን ለክህነቱና

(ካህን ነውና)፣ ከርቤ ደግሞ ለሞቱና ለሕማሙ ነው የሚለው የሊቃውንቱ ትርጓሜ መረዳት የሚቻለው የማዕድናቱንና የዕፀዋቱን አገልግሎት በመረዳት ነው። (ማቴ. ፪፥፲፩)

"እናንተ የምድር ጨው ናችሁ"፦ ሲባልም የጨውን ጣዕም ሰጪነትና መበስበስን መከላከያነት ማወቅ የክርስቲያንን ሚና ይገልጻል።(ማቴ ፭፥፲፫)

፯. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው የመጀመሪያዎቹ ቋንቋዎች ጥናት (Biblical Languages)

ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ (ጥቂቱ በአረማይክ)፣ አብዛኞቹ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። ወደ እኛ የመጣው በግእዝና በአማርኛ ተተርጉሞ ነው።

ጥቅሙ፡- አንዳንድ ጊዜ በትርጉም ምክንያት የሚፈጠሩ ጥቃቅን ብዥታዎችን ለመቅረፍ የመጀመሪያውን ቋንቋ ፍቺ ማየት ይጠቅማል። ለምሳሌ፡- ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ "ትወደኛለህን?" ብሎ ሦስት ጊዜ ሲጠይቀው በግሪኩ መጽሐፍ የተጠቀሙት ቃላት "አጋፔ" (ፍጹም ፍቅር) እና "ፊሊያ" (የወንድማማችነት ፍቅር) በመሆናቸው፣ በቅዱስ ጴጥሮስና በጌታችን መካከል የተደረገውን የፍቅር ደረጃ ልውውጥ ይበልጥ እንድንረዳ ያደርገናል። (ዮሐ. ፳፩፥፲፭)

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ መሠረታዊ ነገረ መለኮታዊ መልእክቱ እንዳንስት አውዱን ጠብቀን በጥንቃቄ ማንበብ ይገባናል እንጂ ፊርተን ብንሸሽው መልካምና ክፉውን መለየት አንችልም። ስለዚህ ከክፉ ለመራቅ፣ በጎውን ለመፈጸም ቃሉን ማንበብ የግድ ነውና በዚህ በክረምት ወራት ጠንክረን ቃሉን እናንብብ።

# ክረምቱን በምን?

በዶ/ር ሜሮን ቶሎሳ

ዛሬ ቀኑ እንደወትሮው "ጪው… ጪው…" በሚል ለጆሮ በሚመች የአዕዋፍ ዝማሬ ሳይሆን፣ የውኃ ጠብታዎች በዕንቊ ላይ እንደሚንጠባጠቡ ሆኖ "ተቅ… ተቅ… ተቅ…" እያለ በሚሰማው በዝናቡ መልእክተኞች እና በጣሪያ ቆርቆሮ መካከል በነበረው የሰላምታ ልውውጥ ነበር።

ይህን ስትሰማ ሶስናም ከሞቀ አልጋዋ ተነሣችና የክፍሏን መስኮት መጋረጃ ገለጥ አድርጋ የጨለመውን ሰማይ ተመለከተች ዝናቡም ጫን ብሎ ቀጠለ ሰማዩ ማሕፀኑን ከፍቶ የያዘውን ማዕበል በአንድ ጊዜ ሲለቀው የዝናቡ ድምፅ ተቀየረ። አሁን በጣሪያው ላይ የሚሰማው ድምፅ የሚወርድ ውኃ ሳይሆን "ሽሽሽ…" እያለ ሲሰማ በሺዎች የሚቆጠሩ ፈረሰኞች በጋሻና በሰይፍ ቆርቆሮውን እየመቱ የሚጋልቡበት ታላቅ የጦርነት ሁካታ መሰለ።

ሶስና የገለጠችውን መጋረጃ እየመለሰች በሐሳቧ "ገና ከመጀመሪያው እንዲህ ከሆነ በዚህ ዓይነት ዘለቅናታ" ብላ ስታውጠነጥን ድንገት ተናገረች። ወዲያው በቅፅበት "ሆይ! ምን ነካኝ! በባዶ ሐሳብ እደክማለሁ እንዴ?" ብላ ራሷን ስትገሥጽ ለእርሷ የምታወራ አይመስላትም ነበረ።

ሶስና ከጓደኛዋ አፎሚያ ጋር ይህን የክረምት ወራት እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው ዕቅድ ሊያወጡ ለጠዋት ስለተቀጣጠሩ፣ ዝናቡም ያዘነላት ይመስል ትንሽ ረገብ ስላለ፣ እድሏን ለመጠቀም ቶሎ ጉዞዋን ጀመረች፤ አፎምያም ቀድማ ደርሳ ኖሯል፤ በሞቀ ፈገግታ እና በናፍቆት በተዘረጉ እጆች ተቀበለቻት።

ሶስና እና አፎምያ አሥራ አንደኛ እና አሥራ ሁለተኛ ክፍል አንድ ወንበር ላይ ተቀምጠው የተማሩ፣ የቅድመ ግቢ ጉባኤ መርሐ ግብርም አብረው ሲሳተፉ የነበሩ ሲሆን የተለያየ ግቢ ጉባኤ መመደባቸው ጓደኝነታቸውን ያላደበዘዘው የልብ ጓደኛሞች ናቸው፡፡

በዝናብ አለፋሁሽ፤ እንግዲህ ሶሲ ይቅር በይኝ! ያው እንደነገርኩሽ ወደ ክፍለ ሀገር አያቶቼን ለመጠየቅ ስለምሄድ ነው፡፡" አለቻት፡፡

ሶስናም ያንን የሚያምረው ፊቷ እንደ ጽጌረዳ ፈክቶ "ኧረ የምን ይቅርታ አመጣሽብኝ ደግሞ! በጊዜ ወደሥራችን መግባት አለብን እኮ! ቀኑ እንደሆነ ነጋ ብለሽ ሳትጨርሺ ይመሽ ጀምሯል፡፡" ብላ መለሰችላት፡፡

"አፎሚ በዚህ በክረምት እረፍታችን ታስታውሺ እንደሆነ እነሰሎሞን ሲሳተፉበት የነበረው የወጣቶች እርዳታ ክበብ ትንሽ ተዳክሟል፡፡ እናም ከነሱ ጋር ተደዋውለን በደንብ የማጠናከር ሥራ ብንሠራ ብዬ አስባለሁ፤ በዋነኝነት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካራ እንዲሆኑ ሥራዎችን መሥራት ከእኛ ብዙ ይጠበቃል፤ ለሥጋ የሚሆን ምግብ የሚመግብ በሰውም ሆነ በፈጣሪያችን ዘንድ ምስጉን ቢሆንም፣ የነፍስ ምግብ በሚመግበው አብልጦ እንደሚደሰት፣ እነርሱን አብልጦ እንደሚወድ አምላካችን "ማርያምስ የማይቀሟት በጎ እድልን መረጠች፡፡" ብሎ ያመሰገናትን ልብ ማለት ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ወንድሞችና እኅቶችን በማስተባበር የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ላይ ለመሥራት ሐሳብም አለኝ፡፡ ዘመናችን በስልካችን ውስጥ እየተሽከረከረች ያለችበት ወቅት እንደመሆኗ እነዚህን ሐሳቦች ተደራሽ ለማድረግ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በአግባቡ መጠቀም እንዳለብንም ልብ ይሏል፤ ከሁሉ በፊት ግን ያው ሰው ፊት ስትቀርቢ ታጥበሽ፣ ንፁሕ ልብስ ለብሰሽ፣ ከቻልሽም ጥሩ መዓዛ ተላብሰሽ አይደል? እነዚህን እኅት ወንድሞች ከማስተማር

በፊት መልካም መዓዛ የተላበሰ መልእክት ለማስተላለፍ የሁሉ መሠረት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁም የወጣትነት ሕይወት የሚዳስሱ መጻሕፍቶችን ማንበብ እንደሚኖርብኝ አልዘነጋሁም። እኔጋ እግዚአብሔር ቢፈቅድ በእረፍት ጊዜያችን ለመተግበር አቅደን መነሣት ይኖርብናል" ብዬ ያሰብኳቸው ዕቅዶች እነዚህ ናቸው፤ አንቺስ ምን አሰብሽ?" ብላ በረጅሙ እየተነፈሰች እንደመጋበዝ በዓይኗ አተኩራ ተመለከተቻት።

አፎሚያም ተቀብላ "ድሮም እኮ ታስደንቂኝ ነበር ሶሲ፤ እውነት ጥሩ ዕቀድ ዐቅደሻል እኅቴ፤ እኔም እንደአንቺ እቅድ ሰፋ ባይልም ሁለት ነገሮችን ለማከናወን አቅጃለሁኝ፤ እኔ ልጅ እንደምወድ ታውቂያለሽ! እንደእድልም ሆኖ እነሱም ይቀርቡኛል፤ አምላካችን "ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው" ብሎ እንደተናገረው (ማቴ. ፲፱፥፲፬) መልካም ትውልድ ለመቅረጽ ከመሠረቱ መሥራት ስለሚያስፈልግ ክፍለ ሀገር አየቶቼ ጥየቃ ስሄድ በዚያውም በሰፈሩ የሚገኙ ሕፃናት ልጆችን ሰብስቤ ወደቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ፣ መሠረታዊ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲማሩ፣ ሃይማኖታቸውን እንዲያውቁ፣ መዝሙር እንዲያጠኑ የማድረግ ሐሳብ አለኝ።" አለች።

ሶስናም ቀበል አድርጋ "አብዛኞቻችን ወጣቶች ላይ ነው ትኩረት የምናደርገው አንቺ ግን ጥሩ አስበሻል፤ ወደ ልጆችም መመልከት ያስፈልጋል፤ ማን አለ ታዲያ የሚያግዝሽ?" አለቻት።

አፎሚያ "ወንድሞች፣ እኅቶች እንዲሁም ዲያቆናትም አሉ፤ እንዲያውም ሌላኛው ሐሳቤ እነሱን በማሰባሰብ በፕሮግራም በየገጠር አብያተ ክርስቲያናት እየሄዱ እንዲቀድሱና በሌሎች አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ ነው።" ብላ መለሰችላት

"መልካም አስበሻል ውዴ ግን ልጆቹን ስታሰባስቢ የወላጅ ፈቃድ ማግኘት ፈተና ሊሆንብሽ እንደሚችል መቼም በሐሳብሽ ይዘሻል።

አብዛኛው የክፍለ ሀገር ልጅ ወላጆቹን በሥራ ስለሚያግዝ ብዬ ነው።" አለች ሶስና።

"እሱንማ እንዴት አላስብም ብለሽ ነው! ከጭቃው እና ከዝናቡ እንዲሁም ከወንዝ ሙላቱ በተጨማሪ ፈተና ሊሆንብኝ እንደሚችል አስቤአለሁ፤ ስለሆነም ቅድሚያ እነሱን ማሳመን እንዳለብኝ ነው ያሰብኩት፤ እንዲከናወንልኝ ደግሞ አምላኬን በጸሎት እጠይቀዋለሁ፤ ከጸሎት ምን ያልፋል ብለሽ ነው?" ብላ በጥያቄ ጀምራ በጥያቄ መልክ ሐሳቧን ገለጸችላት።

ሶስናም "አልጋ በአልጋ እንደማይሆን እያሰብን መጓዝ አለብን ብዬ ነው የኔ ብልህ! በዪ ወደቤት እንሂድ፤ ቆንጆ ቁርስ ሠርቼ ላብላሽ፤ ትዝ ይልሻል ዐሥራ አንደኛ ክፍል ሆነን እንጀራ መጋገር አልችልም ስልሽ የተቆጣሽኝ? ቻልኩ እኮ፤ አሁን ብታዪ ባለሙያ ሆኜልሻለሁ፤ ሙሉ ሴት እየሆንኩልሽ ነው። እኔ የምሠራውን ምስር ወጥ ብትቀምሺ ዶሮ ለምኔ! ያስብልሻል፤ የፍርፍሩ ሳይነሣ ማለት ነው፤ ዶሮ ወጡን ደግሞ አሁን ለእንቊጣጣሽ ሲኦሲ (COC) ፈተና አለኝ!" ብላ ፈገግ አደረገቻት።

አፎምያ እንደ በረዶ የነፁ ጥርሶቿን ገለጥ አድርጋ "ጣቶቼ ተቆረጠሙ በይኛ! ዛሬ ጉዴ ነዋ! ጎበዝ ምክር ሰሚነሽ እባክሽ! እንደእኔ አመለካከት ሴት ልጅ ለራሷ የሚሆን ምግብ የማብሰል ልምድ ሊኖራት ይገባል ብዬ ስለማምን ነው ያኔ ጠንከር ያለ ሂስ የለገስኩሽ፤ በይ እንሂድ እስከምቀምሰው ጓጉቻለሁ።" ብላት ተያይዘው ወደሶስና ቤት አመሩ።